ክፍል ሁለት ማኅበራዊና አስተዳደራዊ ግንባታ

ነህምያ ምዕራፍ 4

ውጪያዊ ተግዳሮት

በነህ. 3 ሥራውን ለመሥራት የተባበሩትን፥ የተሳተፉትን ሰዎች ዝርዝር ተመለከትን። ሥራው ግን እንዴት እንደተካሄደ፥ የተፈጠሩት ችግሮችና ለችግሮቹ የተደረጉት መፍትሔዎች በምዕራፍ 4 እና 5 ነው የሚገኙት።

በምዕራፍ 4 ውጪያዊ ጠላት ነው ሲጋፈጡ የምናየው። ወደ ምዕራፍ 5 ስንዘልቅ ውስጣዊ ችግር ነው። በምዕራፍ 4 የምናገኛቸው የውጪ ጠላቶች ቀደም ብለን በምዕራፍ 2 ያየናቸው ሰንባላጥና ጦቢያ ናቸው። ነገር ግን ሁለቱ ብቻቸውን አይደሉም። ሁለቱ ብቻ ቢሆኑ ኖሮ ነህምያ ሕዝቡን ሁሉ እንደ ሠራዊት አያንቀሳቅስም ነበር። ጠላት ሲሻው በጥቂት ቁጥር፥ ሲሻው ደግሞ እንደ ጭፍራ መነሣት ይችላል። ነህምያም እንደ በሳል፥ አምላኩን የሚያውቅ፥ ሕዝቡን የሚወድ መሪ ተገቢ ነገር ሲያደርግ ይታያል።

1. መለዮ ቀያያሪ መሪ

ነህምያ ባርኔጣውን የሚቀያይር መሪ ነው። ቀድሞ ጠጅ አሳላፊ ነበር። የአሳላፊ የደንብ ልብስ ነበር ልብሱ። ሲመጣ ባለ ራእይ መሪ ነው። አሁን ደግሞ ግንበኛና መሐንዲስ ነው፤ በዛሬ ዩኒፎርም ብንመነዝረው ካኪ ልብስና የፀሐይ ኮፊያ ሳያደርግ አይቀርም። እንደገና ደግሞ የጦርነት ጊዜ መሪ ነው፤ መሪም ነው ጦረኛም ነው። ጦር ሲሰለፍበት የግንበኛ ልብስ ላይ የኮሎኔል ወይም የጀነራል ቆብ ሳይደፋ አይቀርም። መሪዎች እንደዚያ ናቸው።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ፎቶዎች ሳይ ይገርመኝ ነበር። ቡሽ ባርኔጣና የደንብ ልብስ፤ ሙሉ ሱፍ ልብስ፥ አንዳንዴ የባሕር ኃይል አዛዥ የማዕረግ ልብስ፥ የጠቅላይ ጦር አዛዥ የማዕረግ ልብስ፥ ካባ የተደረበበት የአገር ባህል ልብስ፥ ዓይነቱ ብዙ ነው። አንዳንዴም የንጉሥ ባለ ፋሽን ይመስሉኝ ነበር። ለምን? መሪ ነበሩ። ሁሉም በጊዜው ነው የሚለበሰው። ለሲቪል ጉዳይ ትምህርት ቤት ሲጎበኙ፥ ባንክ ሲመርቁ ወዘተ፤ ሲቪል ይለብሳሉ፤ አገሪቱ ተወርራ ለአቤቱታ ወደ ጄኔቭ ሲሄዱ በኢትዮጵያ ባህላዊ ልብስ ላይ የጎዘን ካባ ደርበው ነበር። ሲመለሱ የጦርነት ጊዜ ነውና የጦር አዛዥ የሜዳ ልብስ ነበር የለበሱት፤ መኮንኖችን ሲመርቁ የከፍተኛውን ማዕረግ ደንብ ልብስ ይለብሳሉ። ጀነራሉን ለመመረቅ ከጀነራል መብለጥ አለባቸው። ነህምያም ብዙ ዓይነት መለዮ ያለው ሰው ነው።

መሪ ተፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ሁሉ የሚገባ ጎዶሎን የሚሞላ ሰው ነው። ሁሉን አዋቂ አይደለም። አንዳንድ መሪዎች ሁሉን አዋቂ ሊሆኑ ይሞክራሉ። እነርሱ ባይኖሩ ሕዝቡና አገሪቱ እንደማትኖር ያስባሉ፤ ያሳስባሉም። ግን አገሪቱ ትኖራለች። እነዚህ ራሳቸውን

በራሳቸው የሞሉ ሰዎች ናቸው። ለራሳቸው ያለልክ ቦታና ግምት የሰጡ፥ ያለልክ ዋጋቸውን ያናሩ ሰዎች ናቸው።

አንድ ሰው የቡድን የችሎት ዳኛ (juror) ሊሆን ወይም ለችሎቱ (Jury) አባልነት (ከ3-9 ሰዎች የሚሰየሙበት የዜጋ ዳኞች ቡድን ማለት ነው) ተጠራና ዳኛውጋ ቀረበ። ዳኛው የተለመዱ ጥያቄዎች አቀረበለት። ዳኛው መጀመሪያ ሲጠይቀው፥ "Juror ሆነህ እንዳታገለግል የሚያስገድድህ ምክንያት አለህ?" አለው።

ሰውየው፥ "አዎን ጌታዬ፥ ከሥራ ቦታ ለዚህ ያህል ቀናት መቅረት አልችልም" አለው።

ዳኛው፥ "ለምን? አንተ ባትኖር የቀሩት ሰዎች ሥራውን ሊሠሩት አይችሉም?"

ሰውየው፥ "መቻልስ ይችላሉ፤ ያለኔ መሥራት እንደሚችሉ እንዲያውቁ አልፈልግም።" አለው። ነህምያ እንዲህ ያለ ሳይሆን አሳታፊና ተሳታፊ መሪ ነው። ነህምያ የራሱን ቁርበት በራሱ ማንነት ጥቅጥቅ አድርጎ የሞላ መሪ አይደለም። መለዮ ቀያያሪ መሪ ከራሱ በላይ ማየት የሚችል መሪ ነው።

2. ጦርነት አለ። ሥራና ጦርነት አይለያዩም፤ ጉዞና ውጊያ አይለያዩም። ሁለቱም እኩል ተከናወኑ።

በመጀመሪያ፥ ጦርነት የሚኖረው ለምንድርነው? ብለን መጠየቅ አለብን። ጦርነት በሁለት ምክንያቶች ሊኖር ይችላል። <u>አንደኛው</u> ጠላት በመኖሩ ነው። ጠላትነት ከሌለ ጦርነት አይኖርም። ጠላትነት ካለ ግን ሁሌም ማጥቃትና መጠቃትና መከላከል ይኖራል። ደካማም ኮሳሳም ተገኝ ቢኮን ወጊ መውጋቱ አይቀርም። ተወጊም መከላከሉና ማቄሙ አይቀርም።

<u>ሁለተኛው</u> የጦርነት ምክንያት እርምጃ መወሰዱ ነው። ጠላት ስላለ ብቻ፥ ተስፋፊና ወራሪ ስለኖረ ብቻ ውጊያ አይኖርም። እምቢ የማለትና ከዚያም የማለፍ እርምጃ ሲኖር ግን ውጊያ ይኖራል። እንግሊዞች ግብጽ ወይም ሱዳን ሲገቡ ብዙ ፍጅት አልነበረም፤ ጣሊያኖች ኢትዮጵያ ሲገቡ ግን ፍጅት ነበር። ለምን? እምቢ ስለተባሉ። ኢጣልያና ኢትዮጵያ በአቅም አይመጣጠኑም ነበር። እዚህ ግን እንቢ፥ አሻፈረኝ የሚል መጠቃትና መገዛት የማያውቅና የማይወድ ሕዝብ ነበረና ቅኝ ገዢነቱ አልዘለቀም። 5ቷ ዓመትም ለጣሊያን የጭንቅ ነበረች። ሕዝብ ሁሉ እሺ ብሎ እጅ ቢሰጥ ኖሮ ጦርነት አይኖርም። እሺ ብሎ እጅ ከሰጠ በኋላ ደግሞስ ጫካ ገብቶ የአርነት ንቅናቄ ቢጀምር ሰላም ይኖራል? እርምጃ ሲጀመር ጦርነትም ይጀመራል። ነህምያ መጥቶ፥ መሬት ገዝቶ፥ የራሱን ቤት ሠርቶ፥ እየነገደ ወይ እያረሰ ብቻ ቢቀመጥ ጦርነት አይኖርም። መንፈሳዊ ግንባታም ልክ እንደዚያው ነው።

የጌታ ሥራ ሲሠራ ያለ ተቃውሞ ይሠራል ማለት የዋኅነት ነው። ሰላም የሰፈነበትና ትልቅ የሕንጻ ሥራ የተሠራበት አንድ ዘመን ብቻ ነበረ። ያም ቤተ መቅደሱ የተሠራበት የሰሎሞን ዘመን ነው። 2ዜና 22፥9 እንዲህ ይላል፥ *እነሆ፥ የዕረፍት ሰው የሚሆን ልጅ ይወለድልሃል በዙሪያው ካሉ ከጠላቶቹ ሁሉ አሳርፈዋለሁ ስሙ ሰሎሞን ይባላልና፥ በዘመኑም ሰላምንና*

ጸጥታን ለእስራኤል እሰጣለሁ። በዳዊት ዘመን በፈቃዳቸው ሰጡ፤ 1ዜና 29፥9። በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት አንጻራዊ ሰላም ነበረ፤ ሕዝቡ ግን ይጨቆን ነበር፤ በሰሎሞን ዘመን ግን ቀንበር በሕዝቡ ላይ ተጭኖ፥ አገዛዝ በህዝቡ ላይ ከብዶ ነበር። ኋላ ለመከፈሉ ምክንያት የሆነውም ይህ ነበረ፤ 1ነገ. 12፥4-14። ቢሆንም በሰሎሞን ዘመን በአገሩ ሰላም ነበረና መቅደሱ ተሠራ። ከዚያ ጊዜ በቀር ለአይሁድ የረዘመ ሰላም ኖሮ አያውቅም።

ይህ ውጊያና የሰላም እጦት የሰላሙ ንጉሥ እስኪመጣ ድረስም ይቀጥላል። ይህ ውጊያ ታዲያ የውስጣችንን ሰላም አይነካም። ሰላምን ሊሰጠን፥ ሰላሙን ሊተውልን ጌታ ቃል የገባውን ፈጽሞአል። ግን መንፈሳዊው ውጊያ እስክንሞት አይሞትም። ደግሞም መንፈሳዊ ጦርነት መንፈሳዊ ስለሆነ፥ ወይም ሥጋዊ ተጋድሎ ስለሌለበት ቀላል አይምሰለን። ጠመንጃ ስለማናነግት፥ ኮዳ ስለማንጉተራስ፥ ደም ሲፈስ ስለማናይ፥ በቪድዮ እንደሚጫወቱት ያለ የጨዋታ ጦርነት አይምሰለን።

ጳውሎስ መጋደል ይለዋል። በፊል. 1፥30 *በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፥ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና* አላቸው።

ለቆላስይስ ሰዎች፥ *ስለ እናንተና በሎዶቅያ ሰላሉት ፊቴንም በሥጋ ሰላላዩት ሁሉ እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና* አለ፤ ቆላ. 2፥1።

ለጢሞቴዎስ እንደ በጎ ወታደር መከራ ስለመቀበል ያስተምራል፤ በ2ጢሞ. 2፥1-4። ወታደር ሲባል የሚታየን የመጀመሪያ ነገር የታጠቀ፥ ሊያጠቃ፥ ሊከላከል፥ ሊገድል፥ ሊሞት፥ ሊቆስል የተሰናዳ ሰው ነው። በተለይ በ1ጢሞ 1፥18 *ጢሞቴዎስ ልጄ ሆይ፥ አስቀድሞ ስለ አንተ እንደ ተነገረው ትንቢት፥ በእርሱ መልካም ጦርነት ትዋጋ ዘንድ ይህችን ትእዛዝ አደራ እሰጥሃለሁ* አለ። ክርስትና ጦርነት ነው፤ አገልግሎት ጦርነት ነው። መጋደላችን ከሥጋና ደም ጋር አይደለም፤ ኤፌ. 6፥10-20። ይሁን እንጂ መጋደል ነው። መሣሪያችንም ሥጋዊ አይደለም፤ 2ቆሮ. 10፥3-6። ግን የጦር መሣሪያ ነው።

3. የጦርነቱ ስልት

በጦርነት ጊዜ ዝም ብሎ ወደ ሜዳ መግባት የለም። ምክር ይደረጋል፤ ስለላ ይደረጋል፤ እቅድ ይነደፋል፤ ዕቅድ ሀ ባይሠራ ዕቅድ ለ፥ ያ ባይሠራ ዕቅድ ሐ እየተባለ ይነደፋል። ማጥቃቱ እስከ ምን፥ መከላከሉ እስከ ምን፥ ማፈግፈጉ እስከምን እየተባለ ስልት ይወጣል። ይህ በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ይደረጋል።

ሀ. የነሰንባላጥ የውጊያ ስልት

በነጦቢያ በኩል የጦርነቱ ስልት ማላገጥ፥ ቁ. 1፤ ንቀት፥ ቁ.3፤ ብስጭትና ቁጣ፥ ቁ፥ 1 እና 7፤ የማሸበርና የማስደንገጥ ዘመቻ፥ ቁ. 8፤ ሴራና ጎቡዕ ማስደንገጫ፥ ቁ. 11። ሁሉም አንድ ላይ ሲደመር እንደሚያገሳ አንበሳ መዞር ነው። አይገርምም? ከዚህ በላይ አቅም የላቸውም። ባለፈው በምዕ. 2 ተመሳሳይ ነገር አየን፤ ዋና መሣሪያቸው ንቀትና ፌዝ ነበር።

በተመሳሳይ መንገድ ጠላታችን ሰይጣን በእኛ ላይ የሚያደርገው ወረራ ቢበዛ ድንበሩ የታወቀ ነው። ሰይጣን ኢዮብን በከሰና ባጠቃ ጊዜ እስከተፈቀደለት ድረስ ብቻ ነበር ሊመታ የቻለው፤ ኢዮ. 1፥12 እና 2፥6።

ለ. የነህምያ የመከላከል ስልት

የመጀመሪያው፥ ጸሎት ነው (አምላካችን ሆይ)፥ ቁ. 4-5 እና 9። ጸሎት፥ እግዚአብሔርን መጥራት የእግዚአብሔር ሰው የአካላዊም የመንፈሳዊም ውጊያው ዋናው ስልት ነው። ቁ. 4-5 ያለው የበቀል ወይም የመርገም ጸሎት ነው፤ ይህ አዲስ ኪዳን አይደለምና ይህን ቢያደርግ መገረም የለብንም። በብሉይ ኪዳን እንዲህ ያሉ መዝሙሮችና ጸሎቶች ይገኛሉ፤ ለምሳሌ፥ መዝ. 59፥ 137።

የኛን የውጊያ ስልት በተመለከተ ስልታችን ጸሎት ብቻ ነው። ነህምያ ከሚታይ ሠራዊት ጋር ሊጋፈጥ ስለሆነ በአካልም ዝግጅት አደረገ። የኛ ጠላት ግን የማይታይ ነው፤ ሥጋና ደም አይደለም። መሣሪያችንም ሰይፍና ጦር፥ ሽጉጥና ጠመንጃ፥ መድፍና ታንክ፥ ሚሳይልና አውሮፕላን አይደለም። ምሽግን ለመስበር ግን ብርቱ ነው! ነህምያ በሚታይ ሠራዊት ስለተከበበ ዝግጅቱ በሁለቱም በኩል ነው።

እንደ ብርቱ አዝማች የወሰዳቸው ትክክለኛ ውሳኔዎች ይታያሉ። እነዚህ ጉልሆቹ ናቸው፤ በአንጻራቸው ጠባቂዎች በቀንና በሌሊት አደረገ፤ ቁ.9፤ አስታጥቆ በየወገናቸው አቆመ፤ ቁ. 13፤ ማበረታታትና ማደፋፈር፥ ቁ.14፤ ሥራና ጦርነትን ማቀናጀት፥ እኩሌታን ለሥራ፥ እኩሌታን ለጥበቃ አከፋፈለ፤ ቁ. 16 እና 21፤ በአንድ እጅ ሥራ በሌላ የጦር መሣሪያን አስያዘ፤ ቁ. 17-18፤ በቀውጢ ሰዓት ለውጊያ መሰባሰብን አዘዘ፤ መለከት ወደሚነፋበት ከተት ሠራዊት እንዲደረግ ተናገረ፤ ቁ. 19-20፤ የጦር ሜዳውን (የጦር ቀጣና፥ የጦር ወረዳ) ትኖ አለመሄድ፥ ቁ. 22፤ እንደመሪ ከሠራዊቱ አለመለየትና ለምኞት አለመጨነቁ ይታያል፤ ቁ. 23። [የጥንቱን ልማዳዊ ጦርነት ስናስብ አንዳንዴ መሪ ከኋላ መሆን ያለበት ጊዜ ይኖር ይሆናል - እንዳይሞትና ሠራዊት እንዳይበታተን። ዐፄ ዮሐንስ የሞቱ ጊዜ ጦሩ በአንዴ እንደተፈታ እንዳይሆን። ግን እውነተኛ አዝማች እመሃል ገብቶ የሚዋጋና የሚያዋጋ ነው።] ልብስ ሳያወልቁ ዝግጁ ሆኖ ማደር፤ ቁ. 23። ንቃት፥ ዝግጅት፥ አለመዘናጋት። ጌታ እነጴጥሮስን ይዞ ሄዶ ለአንዲት ሰዓት እንኳ እንዲተጉ ነገራቸውና ራሱ መትጋት ጀመረ። እነርሱ ግን ተኙ። አንዲት ሰዓት እንኳ መትጋት አልቻሉም። ያልተኛው ፈተናውን አለፈ፤ የተኙት ወደቁ። ጦርነትና እንቅልፍ አብረው አይሄዱም።

ሐ. የነህምያ የውጊያ ጥንቃቄ

ጦርነት ማንም ከማንም የማይተዋወቅበት ድፍርስ ግርግር አይደለም። ጠላት ተለይቶ መታወቅ አለበት። ጠላት በመልክ ይለያል፥ በደንብ ልብስ ይለያል። አንዳንዴ የምስጢር ቃልም ይነገራል። ያለዚያ ጉዳቱ ይከብዳል፤ ነህ. 4፥11 *ወደ መካከላቸው እስክንመጣና*

እሰከንገድላቸው . . . ሉያዩም፥ ሉያውቁም አሉ። ወደ መሃል ጠላት የሚገባው ወይ ተኝተን ነው፤ ወይም ወገን መስሎ ነው። ስለዚህ ወገን ተለይቶ መታወቅ አለበት። ጠላት ተለይቶ መመታት አለበት። ያለዚያ ወገንህን ታጠቃለህ፤ እንዲህ ያለውን ጥይት የወገን ጥይት (friendly fire) ይሉታል።

አንድ በቅርብ የማውቀው እና የመዘምራን ቡድናችን አባል የነበረ የጦር አብራሪ ወንድም በወገን ሚሳይል ተመትቶ ወድቆ ነበር። ለጥቂት ጊዜ ሆስፒታል ገብቶ አገግሞ እንደገና ወደ አብራሪነቱ ተመለሰ፤ በግዳጅ ላይ እያለ የሞቱ ወሬ ደረሰን። አሁን ስለሞተ በምን እንደተመታ አላወቅንም። አንዳንዴ ጠላት ያገኘን መስሎን የራሳችንን ወገን እንመታለን።

ኢሕአዴግ በገባ በመጀመሪያ ዓመታት አዲስ አበባ ስታዲየም ተደርጎ በነበረ አንድ ኮንፍራንስ ላይ ኦርቶዶክሶች ተደባልቀው ገብተው መረበሽ ጀመሩና ግርግር ተፈጥሮ ነበር። አንድ ጓደኛዬ አጠገቡ የነበረውን አንዱን ወዲያ ወዲህ የሚል ሰው በረጅምና የሚወራጭ እጁ (ባለextension እጅ ነው የምንለው) በጠረባ ብሎ ጣለው! አስተናጋጆች ዱሮ የደርግ ወታደር፥ አየር ወለድ፥ እና የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የነበሩ ሰዎች የነበሩ አዳዲስ ክርስቲያኖች ናቸውና የጦሩ ስሜት ገና ጨርሶ አልለቀቃቸውም። ወዲያው አጥፈው እንደማይነቃነቅ አድርገው ገትረው ያዙት። ሲናገራቸው በቋንቋው ለዩት እንጂ ጭነው ለፖሊስ ሊያስረክቡት ነበር። ወገንን እና ጠላትን ለይተን ካላወቅን የምንዋጋውን አናውቅም።

በመንፈሳዊ ጦርነትም ነገሩ ተመሳሳይ ነው። ጠላት የሚመስሉ ሰዎችን እና ከሰዎች ጀርባ የሚሠራ ሰይጣንን ለይቶ ማወቅ ጥበብ ነው። ጊዜ ጌታ ጴጥሮስ፥ *አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤* ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሲገሥጸው፥ *ወደ ኋላዬ ሂድ ሰይጣን* አለው፤ ማቴ. 16፥22-23። ጳውሎስም በ2ቆሮ. 2፥6-11 በተለይ ቁ. 11 *በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና* ይላል። የሰይጣንን አሳብ ስተው ይህን በደለኛ ወንድም ይቅር ባለማለት ከልክ ያለፈ ቅጣት አድርሰው አስጨንቀውት ነበር። አንዳንዴ እሳት ያጠፋን መስሎን ነበልባሉን እናጠፋለን። የእሳት ማጥፊያ ስንጠቀም ማድረግ ያለብን ሦስት ነገሮች አሉ። ከሦስቱ ሁለተኛው ዒላማህ የእሣቱ መሠረት ይሁን ይላል (aim at the base of the fire)። ምንጩን ካላወቅን ጳውሎስ እንዳለው ወይ ነፋስ ጎሳሚ እንሆናለን፤ ወይም ወገን ደብዳቢ እንሆናለን።

ጦርነት ሁሌ ማሸነፍ ብቻ ላይኖርበት ይችላል። [ይሄዳል ወታደር ይሄዳል ዘመቻ/ የሚመለከተው ድል ማድረጉን ብቻ/ መሞት አለ መግደል ወይ ይኖራል ምርኮ/ ወታደር ተልኮ። ስዩም ገብረየስ መሰለኝ ጌታውን ሳይከተል በፊት የዘፈነው]። ጦርነት መቁሰል፥ መድማት ያለበት ነገር ነው። ጦርነት ጨዋታ አይደለም። መንፈሳዊ ጦርነት መንፈሳዊ ስለሆነ ቀላል አይምሰለን። ጠመንጃ ስለማናነግት፥ ኮዳ ስለማንንተራስ፥ ደም ሲፈስ ስለማናይ፥ በቪድዮ እንደሚጫወቱት ያለ የጨዋታ ጦርነት አይምሰለን።

ለውይይት መከዮ መቀየር ሲያስፈልግ የምንቀይር አገልጋዮች ነን? ጦርነት ሁሌም አለ። መንፈሳዊ ሕይወትና መንፈሳዊ ጦርነት አይለያዩም፤ ክርስቲያናዊ ጉዞና ውጊያ አይለያዩም። በቅጡ የምንዋጋ ሰዎች ነን? የጦርነት ስልታችንስ እንዴት ነው? የጸሎታችን ቦታ እንዴት ነው? ምሽጋችን የተጠበቀ ነው? የጠላትን አመጣጥ የምናስተውል ነን? ጠላትን ከወገን ለይተን÷ በተለይም ከጠላት ጀርባ ሆኖ የሚሠራውን መንፈስ እናስተውላለን?

ነህምያ ምዕራፍ 5
ውስጣዊ ችግሮች

በነህ. 4 ከውጪ የመነጨ ጠላትና ተግዳሮትን ነው ያየነው። በነህ. 5 ግን ከውስጥ የሚቦረቡሩ ችግሮች ይታያሉ። በጦርነት ጊዜ ያልታሰበና ትልቅ አደጋ የሚያደርሱት 5ኛ ረድፈኞች የሚባሉት ናቸው። 4ቱ ረድፈኞች 4ቱ ማዕዘናት ሲሆኑ 5ኛው ውስጣዊው ነው። አምስተኛ ረድፈኞች የሚባለው ቃል ብዙ ይነገር የነበረው በደርግ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነበር። ከታች ከሱማሌ ከላይ ከኤርትራ በሱዳን በኩል ኢዲዩ አገሪቷን ከወጉት በተጨማሪ ከውስጥ በኢሕአፓ የተሠራው የከፋ ነው ለማለት ነው ይህን ቃል ይጠቀም የነበረው። 5ኛ ረድፈኞች የሚለው ቃል መጀመሪያ የተጠቀሙት እስጳኞች ናቸው። በ1936 በእስጳኞች የእርስ በርስ ጦርነት ጊዜ ማድሪድ ተከብባ ሳለች ከበባውን ያደረገው ጦር አዛዥ ኤሚሊዮ ሞላ ለጋዜጠኞች ሲናገር አራቱ ከበባውን ሲያደርጉ 5ኛው ረድፍ ወይም ዓምድ (በስፓኒሽ Quinta Columna) ከውስጥ ሆኖ መንግሥት ጦሩን በመቦርቦር እንደሚሠራ ተናገረ።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ውጪያዊ ጠላትን መቃወም አይከብደውም፤ የውጪው ሲከፋና ሲጠነክር በአምላኩ ይደገፋል። ዕብ. 11፥34 *የአንበሶችን አፍ ዘጉ፥ የእሳትን ኃይል አጠፉ፥ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፥ ከድካማቸው በረቱ፥ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፥ የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ* ይላል። የባዕድ ጭፍራ ማባረር ከባድ አይደለም። የወገን ጭፍራ ግን ከባድ ነው። እስራኤል ተማርከው ሄደዋል፤ ግን የሄዱት አስቀድሞ ከውስጣቸው ተቦርቡረው ነው።

እስራኤል ከግብጽ ወጥተው ወደ ተስፋዋ ምድር ሲገቡ ጭፍሮችን እያባረሩ ነበር የመጡትና የገቡት፤ የሚያቆማቸው አልነበረም። አንድ ምሳሌ ብንወስድ፥ ዘኁ. 21 ከነዓናዊው የዓራድ ንጉሥ ተነሣባቸው፤ ስእለት ተሳሉ፤ ሁሉን ደምስሰው አገሩን ሔርማ (እርም፥ ውድመት) ብለው ሰየሙ፤ 21፥1-3። ከዚህ በኋላ ግን (21፥4-6) ከውስጥ የአለመርካት በሽታ ይበላቸው ጀመር፤ መናን ተጸየፉ። በእባብ ተቀጡ። ከውጪ ያልተሸነፉ ከውስጥ ተነደፉ። በምግብ ምኞት።

በዚሁ ምዕራፍ (ዘኁ. 21፥21-35) የአሞራውያን ንጉሥ ሴዎንና ሕዝቡና አገሩ፥ ቀጥሎ የባሳን ንጉሥ ዐግና ሕዝቡና ምድሩ እንዴት እንደጠፉ ተጽፎአል። በሚቀጥሉት 3 ምዕራፎች ዘኁ. 22፥23፥24 የሞዓብ ንጉሥ በሦስቱ ነገሥታት የሆነውን ስላየ በጦርነት ከመግጠም የሚሻል መንገድ ይኖራል ብሎ በእርግማን መጣባቸው። በለዓም የሚባል የታወቀ ረጋሚ ጠራባቸው። እርግማን በእስራኤል ላይ አይሠራም፤ አስማትና ምዋርትም የለም፤ 23፥7-8 እና 23። በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እርግማን አይሠራም።

ስለ እርግማን ጥቂት ልበል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተጋንኖ ይሰበክ የነበረና የተጻፈለት የእርግማን ፍርሃት ትምህርት አለ። Generational Curse ይባላል። ዋና አሳቡ፥ ዘር ማንዘራችን የሠራው በደል በኛ ሕይወት ላይም ሰይጣን ሥልጣን እንዲኖረው ያደርገዋል፤

መብት ይሰጠዋል የሚል ነው። በእስራኤል ላይ አስማት ካልሠራ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት በሆንን በእኛ ላይማ ከቶም አይሠራም። ጦርነት አይፈጃቸውም፤ እርግማን አያጠቃቸውም። እርግጥ ወላጆች የሠሩት ጥፋት አካላዊ፥ ወይም ንዋያዊ በሆነ ሁኔታ በቀጣይ ትውልድ ላይ ሊደርስ ይችላል። በዘር የሚተላለፉ በሽታዎች ይኖራሉ። ያለ ኃጢአት የሚመጡ በሽታዎች ቢኖሩም የኃጢአት ውጤቶችም የሆኑ በሽታዎች አሉ። ይህ መርገም ሊባል ይቻላል። አባቴ ንብረቱን ያወደመ ከሆነ እኔ ከ0 ልጀምር ግድ ነው። ጌታን የማላውቅ ከሆንኩ መንፈሳዊ ሕይወቴም ላይ ተጽዕኖ ሊኖር ይችላል። የጌታ ባንሆን ኖሮ በወላጆቻችን የሚሠራ ርኩስ መንፈስ በእኛ ላይ ሥልጣን ሊኖረው ወይም ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

በብሉይ ኪዳን ይህ የትውልድ እርግማን ተደርጎ የሚጠቀሰው ዘጸ. 20፥ 5-6፤ 34፥5-7፤ ዘዳ. 5፥9-10 ነው። በነዚህ ጥቅሶች እርግማን የሚል ቃል አናገኝም። <u>በሚጠሉኝ</u> እና <u>ኃጢአት</u> የሚሉ ቃላት ናቸው ያሉት። ወላጆቻቸውም የማይታዘዙ ነበሩ። ሰዎቹም ራሳቸው የማይታዘዙ ናቸው። ከነዓናውያንን ከአብርሃም ዘመን በኋላ እግዚአብሔር በ4መቶ ያህል ዘመናት ነቅሎ አጠፋቸው። ስለሚታዘዙት የተነገረው ቃልም ትእዛዜን ለሚጠብቁ ተብሎ ነው። ከዚህ በተረፈ በብሉይ ኪዳንም ስለ አባቶች ኃጢአት ልጆች መቀጣት እንደሌለባቸው በኤር. 31፥ 29-30 እና በሕዝ. 18 በሙሉ በግልጽ ተጽፎአል። የጌታ ባንሆን ሊሠለጥንብን የሚችል ኃይል የጌታ ሆነን ግን አይሠራም!

የሚያሳዝነው ግን ከዘጉ. 21-24 ስናያቸው ጦርነት ያላጠቃቸው፥ የበለዓም እርግማንም ሳያጠቃቸው ወደ ባርኮት የተለወጠላቸው እነዚህ በዘጉ. 25 ሲታዩ ከሞዓብ ጋር በማመንዘር ተቀሰፉ። በነቆሮ. 10፥1-13 የተጻፈው ስለ እነዚህ ነው። የውጪው ግፊት ያላንገዳገዳቸው፥ ግን የውስጡ ብክለት ያስደገደጋቸው ሰዎች ናቸው።

የውጪ ነፋስ ገፍትሮ የማይጥለውን ዝግባ ምስጥ በልቶ ቦርቡሮ ይጥለዋል። በልጅነቴ በእርሻ ቦታችን የነበረ አንድ ትልቅ የሾላ ዛፍ ነበረ። ይወድቃል ተብሎ ፈጽሞ የማይታሰብ ትልቅ ዛፍ ነው። ግን አንድ ቅዳሜ ስሄድ ወድቆ አገኘሁት። በኋላ ቀርቤ ሳየው ያስደነቀኝ ውስጡ የተቦረቦረና እንዲያውም ንቦች ማር የጋገሩበት ሆኖ መገኘቱ ነው። ንቦቹን በጢስ አፍነው አባርረው ማሩን ስንበላ ውለናል። ከውጪ ሲታይ ግዙፍ ውስጡ ግን ባዶ። ምን ቦረቦረው? ምስጥ!

ከውጪ አጥንት የሚሰብር እንጂ አጥንት የማይሰብረው ጤናማ ጥርስ አንዳንዴ ከውስጥ በስብሶ ይወልቃል። ምን አበሰበሰው? ታርታር የሚባል ከውስጥ የሚቦረቡር ባክቴሪያ!

በስደትና በመከራ፥ በድብደባና በእስራት ያልተፈቱ ክርስቲያኖች በሰላሙና በምቾቱ ጊዜ ይወድቃሉ። ለምን? በፍላጎትና በምኞት! በሥጋ ፍላጎት፥ በገንዘብ ፍላጎት፥ በሥልጣን ፍላጎት ተይዘው ይጠፋሉ። ለምን? የውስጡ ሰውነት ስላልጠነከረ! ጳውሎስ በኤፌ. 3፥ 14-17 እንዲህ አለ፥ *ስለዚህ ምክንያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፤ በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይሰጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ።* የውስጡ ሰውነታችው በኃይል እንዲጠነክር ጸለየ።

በነህምያ ምዕ. 4 የውጪ ጠላት ተነሣባቸው፤ ግን ንቅንቅ እንኳ አላደረጋቸውም። ደንግጠው ወይም ፈርተው ቅጥሩን መሥራታቸው አልተቋረጠም። ከጠላት ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት ወይም የእርቅ ድርድር አላደረጉም። ቆሙ፥ ታመኑ፥ አሸነፉ። ጠላትም ዛተ፥ ዘበተ፥ አፌዘ፥ ደነፋ፤ ግን ከዚያ ያለፈ ምንም ነገር አላደረገም። እግዚአብሔር አምላኩ የሆነ ሕዝብ የጠላት ሰለባ አይሆንም። ሰይጣን ዙሪያውን እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞረዋል እንጂ አይውጠውም! በነህ. 5 ግን ከውስጥ መበስበስ ሲጀምሩ ይታያል። መበስበሳቸው የቆየም አዲስም ነው። በሕዝቡም በመሪዎችም በኩል ነው። መበስበሳቸው በሁለት በኩል ነው።

1. <u>አንደኛ ውስጣዊ ችግር፥ ሕዝቡ።</u>

ከችግሩ በፊት የችግሩን ምክንያት እንይ። ምክንያቱ የሕዝቡ ከራብና የግብር ገንዘብ ከማጣት የተነሣ እርሻን ቤትን ወይንን አስይዞ ገንዘብ መበደራቸው ነው።

ችግሩ እነዚህ የሚከፍሉትን በማጣታቸው የገዛ ወገኖቻቸው ወለድ ያበድሯቸው ነበር፤ ስለ ዕዳውም ወንድሞቻቸውን ባሪያ ያደርጉና ይይዙ ነበር፤ 1-5። ይህ ለወገን በወለድ ማበደርና ወገንን ባሪያ አድርጎ ማኖር በሕጉ የተከለከለ ነው። ማበደር ይችላሉ፤ ግን ወለድና አራጣ አይጭኑባቸውም። ባሪያ ማድረግ ይችላሉ፤ ግን ቢበዛ ለ7 ዓመት ብቻ። ለዚያውም ሲወጡ ባርከው፥ ሰጥተው፥ ለግሰው ነው የሚሰድዱአቸው። ይህ ሕጉ ነው። ዘጸ. 21፥2-6፤ 22፥25-27፤ ዘሌ. 25፥35-43፤ ዘዳ. 15፥11-17፤ 23፥19-20።

እነዚህ ግን በወለድ እያበደሩ ናቸው። መክፈል ሲያቅታቸው ደግሞ ንብረታቸውን እየያዙ ናቸው። ባለዕዳዎቹን እንደባሪያ አድርገው እያኖሩ ናቸው። ችግሩ ይህ ነው። እንደ ሕጉ እየኖሩ አይደሉም። ቀድሞ እንደ ሕጉ ባለመኖራቸው ምድሪቱ እንደተፋቻቸው ረስተው አሁንም እንደ ሕጉ ሳይሆን ሕግ እንደሌላቸው እንደ አሕዛብ መኖርን እየተለማመዱ ናቸው። ደግሞ የገዛ ወገኖቻቸውን ነው መጠቀሚያና መኖሪያ የሚያደርጉት። በአንድ ወገን አጥተው ነጥተው እርሻቸውን፥ ቤታቸውን፥ ወይናቸውን፥ ልጆቻቸውን አስይዘው የሚበደሩ አሉ፤ በሌላ በኩል እነዚህን መጠቀሚያ የሚያደርጉ አጥንታቸውን የሚግጡ ሰዎች አሉ።

በቤተ ክርስቲያንም እንዲህ ያሉ ይኖራሉ። መንፈሳዊነታቸው መጠቀሚያ የሚያደርጉ፤ ሥልጣናቸውን፥ ችሎታቸውንና ጸጋቸውን፥ ቃል ማወቃቸውን መጠቀሚያ የሚያደርጉ በዚህ ሁሉ ደግሞ ሌሎችን የዋሆችና አላዋቂዎች የሚመዘብሩ ይኖራሉ።

<u>መፍትሔ</u>፤ 6-13 ተግባራዊ እርምጃ። ነህምያ ይህንን ውስጣዊ ብልሽት ለማጥፋት በርካታ ነገሮችን አደረገ።

ተቆጣ። ተቆጣሁ አለ በቁ. 6። መቆጣት ጥፋት የሚሆነው የሚያስቆጣ ነገር ባልኖረበት ሲቆጡ ነው። ተገቢና ትክክለኛ ቁጣ አለ። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ልክ ያልሆነ ነገር፥

በቅዱሳን ሕይወት ውስጥ ትክክል ያልሆነ ምስክርነት ስናይ፥ ስንሰማ ውስጣችን የማይቆጣ ከሆነ ልክ አይደለንም። ነህምያ ተቆጣ። ቁጣ የስሜቱን ሁኔታ የሚገልጥ ቃል ነው።

አሰበ። በልቡ አሰበ፤ ቁ. 7ሀ። በልብ ማሰብ ምንም ነገር ከማድረግ፥ ከመናገር፥ ከመራመድ በፊት መደረግ ያለበት ነገር ነው። አንድን ነገር ሳያስቡ ከማድረግ አስቦ አለማድረግ የተሻለ ነው። አስቦ ካለማድረግ ደግሞ አስቦ ማድረግ በእጅጉ የተሻለ ነው።

ወደ ተግባር ተራመደ። በአፉ ተናገረ፥ ተጣላቸው፥ ጉባኤ ሰበሰበባቸው፤ 7ለ-ነ። የተናገረው ዋና ነገር ደግሞ ምክርና ተግሳጽ ነው፤ ቁ. 9። አሕዛብ እንዳይሰድቡአቸው እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲሄዱ ነገራቸው። የጌታ ሰዎች አካሄድ እግዚአብሔርን ወይ ያስመሰግነዋል ወይም ያሰድበዋል። ሮሜ 2፥24 *በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ሰም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ።* ይላል፤ የተጻፈ የተባለው በኢሳ. 52፥5 ነው። 2ጴጥ. 2፥2 *ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል* ይላል።

ራሱን ምሳሌ አደረገ። ነህምያ፥ አድርጉ ብቻ ብሎ ወደ ጓዳው የገባ ሰው አይደለም። እንደ ፈሪሳውያን የማያደርገውን አድርጉ አላለም። ራሱም ተጨምሮ ተውላቸው ሳይሆን እንተውላቸው ነው ያለው። ደግሞም እባካችሁ እያለ ለመናቸው እንጂ አላስገደደም ቁ. 10-ነ።

ሕዝቡ ታዘዙ፤ ቁ. 12-13። እውነተኛ የጌታ አሠራር ባለበት ቦታ የሰዎች ልብ ይነካል፤ ይለወጣል። ይታዘዛሉ። ታዘዙ።

ለውይይት **ከውጪያዊ ግፊት የምንቆም ነን? ከውስጣዊ መበስበስስ? የውስጥ ሰውነታችን ሸንጋት ነው? በጌታ ቤት ውስጥ መጥፎ ነገር ስናይና ስንሰማ ውስጣችን ይቆጣል? ተቆጥተንስ አልፈን የምንሄድ ነን ወይስ ተግባራዊ ምላሽ የምንሰጥ ነን? በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ከውስጥ ሸየቦረቦረ፥ ሸየበላ ያለ ነገር አለ? ምን ይሆን?በዚህ ውስጥ የመሪዎች፥ የአማኞችም ሚና ምን ሸንደሆነ ሸናስባለን?**

2. ሁለተኛ ውስጣዊ ችግር፥ መሪዎች።

የሕዝቡን ከውስጥ መበላሸት እንዳየን እዚህ ደግሞ መሪዎች መበላሸታቸው ይታያል። እግዚአብሔር የሕዝቡ መሪዎችም እንዳይበላሹ ይፈልጋል። አካሉ ንጹሕ፥ ቤተ ክርስቲያኑ ንጽሕት ሆና እንድትኖር ይፈልጋል። በሐዋ. 5 አንድ ጠንካራና ከባድ ቅጣት ሲፈጸም ይታያል። ሐናንያና ሰጲራ በጽኑ ተቀጡ። መሬታቸውን ሸጠው ገንዘባቸውን ግማሹን ደብቀው ግማሹን አምጥተው አስቀመጡ ንጹሐን መስለው። በሁለት ምክንያት ቅጣቱ የደረሰባቸው ይመስለኛል። <u>አንደኛው</u> ግልጽ ነው፤ እግዚአብሔርን ማታለላቸው ነው። ገንዘባቸውን ከፍለው ማስቀመጣቸው አይደለም። ማስቀመጥ ይችላሉ፤ ሲጠየቁም ይህ ግማሹ ነው፤ ግማሹ እቤት ነው ማለት ይችላሉ። ግን ዋሹ። እንደ ሌሎቹ መስለው መታየት ሞከሩ። አንዱ የቅጣታቸው ምክንያት ይህ ነው። <u>ሁለተኛው፥</u> የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን ገና ከጅምሩ ከአስመሳዮችና ከግብዞች ጌታ ሊያጠራ የወደደበት መንገድ በመሆኑ ነው። የነዚህ አስመሳዮች ሞት ፍርሃት ፈጠረ። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን በቅድስና ማደግ ጀመረች። እግዚአብሔር ሕዝቡ ከውስጥ እንዳይበሰብስ ይፈልጋል።

ሕዝቡ ብቻ ሳይሆኑ መሪዎችም መሪዎች እንዲሆኑ ይፈልጋል። በነህምያ ዘመን መሪዎች ቀንበር አክብደው ነበር። እዚህ የሚታየው መሪ ነህምያ ነው፤ የሆነው ችግር ግን ከነህምያ በፊት የነበሩ መሪዎች የፈጠሩት ችግር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ መሪዎችን እናገኛለን።

አንዳንዶች <u>መጥፎ</u> መሪዎች ናቸው። ለራሳቸው ጥቅም ብቻ የሚኖሩ፤ ለእግዚአብሔር ሕዝብም ለእግዚአብሔርም ደንታ የሌላቸው ሰዎች ናቸው። እንደ አክዓብ፥ እንደ ኢዮርብዓም፥ እንደ ምናሴ ያሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው። አንዳንዶች ደግሞ <u>መልካምና ክፉ ድብልቅ</u> መሪዎች ናቸው፤ ዳዊት ጥሩ ምሳሌ ነው። መልካም መሪ ነው፤ ምልስ ሰው ነው፤ ግን ንጹሕ ደም ያስፈሰሰ ሰውም ነው፤ ለፍላጎቱ ብሎ ኦርዮን አስገደለ። ሲሞትም ለልጁ ለሰሎሞን ያልጨረሳቸውን የቅጣት ፕሮጀክቶች አውርሶ ነው የሞተው፤ 1ነገ. 2፥5-6፤ 8-9። አንዳንዶች መሪዎች ግን <u>ቀናዎችና እግዚአብሔርን የሚፈሩ</u> ናቸው። ሙሴ ትሑት መሪ ነበር። ዲቦራ መልካም መሪ ነበረች። ነህምያ ጥሩ ምሳሌ ነው።

ችግሩ ይህ ነው። በዚህ በነህምያ ዘመን ከነህምያ ቀድመው የነበሩ መሪዎች ነበሩ። የመጀመሪያዎቹ አይሁድ ነህምያ ከመምጣቱ በፊት ከ70 ዓመታት በፊት ከዘሩባቤልና ኢያሱ ጋር የመጡ ነበሩ። ይህ የነህምያ ዘመን ከነዘሩባቤል ብዙ የቆየ ስለሆነ እነ ዘሩባቤል እነ ኢያሱ አሁን ሞተዋል። በፈንታቸው የተተኩት በሕዝብ ትከሻ ላይ ተቀምጦ መፈንጨት የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው።

በሕዝቡ ትከሻ ላይ ሸክም ከብዶ ነበር። ቁጥር 15 *ከእኔ አስቀድመው የነበሩት አለቆች ግን በሕዝቡ ላይ አክብደው ነበር፤ ስለ እንጀራውና ስለ ወይኑ አርባ ሰቅል ብር ይወስዱ ነበር፤ ሎሌዎቻቸውም ደግሞ በሕዝቡ ላይ ይሠለጥኑ ነበር፤ እኔ ግን እግዚአብሔርን ስለ ፈራሁ እንዲህ አላደረግሁም።*

በሕዝቡ ትከሻ ላይ ሸክም ከብዶ ነበር። መሪዎች ሲቀናጡ የቅንጦታቸው ዋጋ ከፋይ ሰፊው ሕዝብ ነው። መሪዎች ከሕዝቡ በራቁት ልክ የሕዝቡ መከራና ጉስቁልና አይታያቸውም፤ አይሰማቸውም።

- ገዥዎች በየቀኑ ምግብና ወይን ያስቀርቡ ነበር።

- በየቀኑ 40 ሰቅል ያስወጡ ነበር። በኛ ትርጉም ይህ *ሰለ እንጀራውና ሰለ ወይኑ ለርባ ሰቅል ብር ይወሰዱ ነበር* በሚለው ውስጥ አይታይም፤ ግን በተጻፈበት ቋንቋ ከእንጀራውና ወይኑ በተጨማሪ መሆኑ ይታያል። ሰቅል የክብደትም የገንዘብም መለኪያ ነው። 40 ሰቅል በአሁን ገንዘብ ሲተመን ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ይቸግራል። ወደ ግማሽ ኪሎ ብር ማለት ነው። የወረቀት ሳይሆን የብረቱ ብር። ግን ቀላል ዋጋ አለመሆኑን ከነህ. 10፥32-33 እንረዳለን። በዚያ ለአንድ ሰው በዓመት የሰቅል 1/3ኛ ነው የተተመነው ለዚያ ሁሉ ሥራ ማስፈጸሚያ። በቀን 40፥ በዓመት ወደ 15ሺህ ሰቅል ነው። ሕዝቡ በዚህ ጊዜ 90ሺህ ነው ብለን ብንገምት በዓመት 30ሺህ ይገባል፤ እነዚህ ከምግብና መጠጥ ሌላ በቀን የዚያን ግማሽ ይወስዱ ነበር ማለት ነው።

- ደግሞም ሎሌዎቹ ይሠለጥኑ ነበር። ይህ ማለት አስገድደው ሕዝቡን ያስከፍሉ ነበር።

የሚሠራው ግፍና በደል ነውና በምዕ. 5 ክፍል አንድ ያየነው የሕዝቡ ችግር ቢፈጠር ምን ያስገርማል? ሕዝቡ የሚከፍለው ቢያጣና በወለድ ቢበደር፥ የተበደሩትን መክፈል አቅቶአቸው እርሻቸውንና ወይናቸውን ቢያስይዙ፥ ባሪያዎች ሆነው ራሳቸውን ቢሸጡና ልጆቻቸውን ቢሸጡ ምን ያስገርማል? መሪዎች በሕዝብ ትከሻ ላይ ሲቀመጡና ሲጨፍሩ ያንን ትከሻ የሚያከሱ ከሆኑ ኋላ ያ የተቀመጡበት ትከሻ እንደሚቆረቁራቸው አላወቁም። አንዳንድ መሪዎች ለራሳቸው ብቻ የሚኖሩ ናቸው።

በዓለም ላይ ብዙ ድኃ አገሮች አሉ። ዋናው ችግር ተፈጥሮ አይደለም። የሰዎች ዳተኝነትና መቦዘንም አይደለም። ክፉ መሪዎች ናቸው ችግሩ። በላተኛ መሪዎች፥ ነቀዝ መሪዎች፥ አግበስባሽ መሪዎች፥ ሰብስቤዎች ናቸው። ከጥቂት ዓመታት በፊት የግብጹ ፕሬዚደንት ሆስኒ ሙባረክ ከሥልጣን ሲወርድ ወደ 70 ቢሊየን ዳለር፥ (70 ሺህ ሚሊየን የአሜሪካ ዳለር ማለት ነው!) አሸሽቶ ነበር ተብሎአል። በዚያኑ ጊዜ አካባቢ (2010) የኤርትራ ጠቅላላ GDP 4.2 ቢሊየን ነው። የኢትዮጵያ 29.7 ቢሊየን ነው። የሁለቱም የ2010 ተደምሮ የ70 ቢሊየን ግማሽ እንኳ አይደርስም። የሊቢያው ጋዳፊ ወደ እንደሚገመተው ከ32-200 ቢሊየን ነበረው። አማካዩን ቁጥር ብንወስድ 116 ቢሊየን መሆኑ ነው። ስግብግብነት በመሪዎች ላይ ሲሠለጥን ክፉ ነው። የብዙ የአፍሪቃና የሌሎችም አገሮች አምባ ገነን መሪዎች ለምንድርነው ሳይሞቱ ወይም ከእነርሱ በጉልበት የሚበልጥ መጥቶ እስኪያወርዳቸው ቦታቸውን የማይለቅቁት? የኮሚኒስት አገሮች መሪዎች (አሁን ቢመነምኑም) ለምንድርነው እስኪሞቱ የማይወርዱት? ከእነርሱ የተሻለ ጠፍቶ ነው? መሪዎች በመጨቆን የሚደሰቱት ለምንድነው?

በቤተ ክርስቲያንም እንደዚያ የመሰሉ መሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ መሪዎችን እንድናከብር ያስተምረናል፤ ዕብ. 13፥7፥17። በሌላ በኩል መልካም ያልሆኑ መሪዎችም ኖረዋል፤ 3ዮሐ፥ 9-10። ተመልከቱ! ተመልከቱ መሪዎቻችሁን። መልካሞች ከሆኑ ምሳሌነታቸውን ተከተሉ። የኑሮአቸውን ፍሬ እየተመለከታችሁ አክብሩአቸው። ሕዝቅኤል እንደጠቀሳቸው እረኞች (ሕዝ. 34) ነቀዞች ከሆኑ፥ ምእመናንን እያከሱ ራሳቸውን የሚያደልቡ ከሆኑ አሁንም ተመልከቱአቸው። በጌታ ቃል ተፈትነው ተመዝነው ወይ ከብደው ወይ ቀልለው ይገኛሉ። ተመልከቱአቸው።

የስግብግብነት ወንጌል የሚሰብኩ ሰባኪዎች በዘመናችን ጉልህ ስፍራ ይዘው ይደመጣሉ። በጣም የሚስብ፥ የሚጥም፥ ለስላሳ፥ ቃል አላቸው። የብልጽግና፥ የጤንነት፥ የስኬት የውሸት ተስፋ ይዘራሉ፤ ይበትናሉ። ከ2008-10 ባሉት ሦስት ዓመታት በአሜሪካ ውስጥ አንድ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የስድስት ክርስቲያናዊ ድርጅቶች የገንዘብ አያያዝና አወጣጥ ተጠርጣሪ ነውና ይፈተሽ ብሎ ኮሚቴ ተሰይሞ ነበር። ምርመራው የስድስቱንም ዋና መሪዎች እጅግ አስደንግጦ ነበር። ሁለቱ እንዲያውም በግልጽ ተቃውመው ይህ እኛን መመርመር የIRS፥ ማለትም፥ የአሜሪካ የአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ሥራ ነው እንጂ የሴኔት ኮሚቴው ተግባር አይደለም ብለው ተናግረው ነበር። በመጨረሻው ውጤት የተጠርጣሪዎቹ ክሳቸው ቢሰረዝም ኪሳቸው እንደደለበ ነው የቀረው። የምርመራው ሂደት የአንዳንዶቹን የገንዘብ አያያዝና አወጣጥ በትንሹም ቢሆን ወደ አደባባይ አውጥቶአል። የአንዳንዶቹ ንብረትና የባንክ ደብተር ከአንድ አናሳ መንግሥት ጋር የሚወዳደር ነው። መሪዎቹ አማካዩ የቤተ ክርስቲያናቸው ምእመን ከሚያገኘው የዓመት ገቢ ከ30-40 እጥፍ በላይ የሚያገኙ ናቸው። በቀላል ግምት አማካዩ ገቢ በወር 3ሺህ ቢሆን እና የመሪዎቹ በወር ከ90ሺህ እስከ 120 ሺህ እንደማለት ነው። ይህ በጣም ቀላሉ ስሌት ነው።

በአገራችንም የሰዎችን ኪስ የሚያራቁቱ ሐሰተኛ ነቢያት እና ሐዋርያት እየበዙ በመጡበት ልክ ይህ እንደሚታይ ምንም ጥርጥር የሌለበት ጉዳይ ነው።

መፍትሔ፤ ቁጥር 14 እና 15ለ-19

ወደ ነህምያ ስንመለስ ችግሩን አየን። መፍትሔውስ? ነህምያ ይህን የአለቅነት ንቅዘት የተቋቋመው በአንድ መንገድ ነው። የአለቃ መብትን በመተውና እውነተኛ የመሪ ምሣሌነትን በማሳየት። እንደ ምሳሌነት ያለ ከመሪ የሚጠበቅ ዓይነተኛ መለኪያ ከቶም የለም። በ2ተሰ. 3፥7-9 ጳውሎስ፥ *<u>እኛን ልትመስሉ</u> እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና፤ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና፤ ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ሰንካ እንዳንከብድበት፥ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ፥ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም። ይህም እኛን ልትመስሉ <u>ራሳችንን እንደ ምሳሌ</u> እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ፥ ያለ ሥልጣን ሰለ ሆንን አይደለም* አለ።

ጴጥሮስም በ1ጴጥ. 5፥1-3 እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፤ <u>ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ</u> ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ አለ።

ነህምያ መልካም ምሳሌ ነበረ። ያደረጋቸውን እንይ፤

- አለቃ የሚገባውን ስንቅ ለ12 ዓመት አልበላንም፤ ቁጥር 14።
- የሆነውን፥ ይደረግ የነበረውን አስተዋለ። የራሱን እርምጃ የተራመደው ግን እግዚአብሔርን በመፍራት ነው፤ ቁጥር 15።
- ሥራው ላይ አተኮረ እንጂ ንብረት የመሥራት፥ እርሻ የመግዛት፥ መዋዕለ ንዋይ የማፍሰስ፥ ንግድ የመነገድና የማስነገድ ተግባር ላይ አልተሰማራም። ትኩረቱ ሥራው ነበር፤ ቁጥር 16።
- ከገበታው የሚበሉ ከ150 በላይ ሰዎች ኖረው መደበኛ ቀለብ ብቻ ይቀበል ነበር እንጂ የአለቃ አበል አይቀበልም ነበር፤ ቁጥር 17-18።
- ስላደረገው ነገር ሲመጻደቅ ሳይሆን አምላኩን ሲማጸን የሚታይ ሰው ነው።

ለውይይት **ነህምያ መልካም መሪ ነበር። የመልካም መሪ መለኪያዎች ከሚባሉት ነገሮች ጥቂቱ ምን ምን ናቸው? ሥልጣን፥ መብት እና ግዴታ ምን ማለት ናቸው? እነዚህ ነገሮች ግንኙነት አላቸው? መሪ ከሥልጣን ጋር ግዴታ አለበት? የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት ያሉ መሪዎች ሊሆኑ ይገባል? መንጋን በምሳሌነት ስለመምራት ሊጠቀሱ የሚችሉ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ይገኛሉ? እኛስ መልካም ምሳሌዎች ነን?**

ነህምያ ምዕራፍ 6

ስልታዊ ሴራ

በነህ. 4 ውጪያዊ ተግዳሮትን፥ በምዕ. 5 ደግሞ ውስጣዊ ችግሮችን ተመልክተናል። በምዕ. 6 ትግሉ ሲያቆም ሳይሆን ሲቀጥል ይገኛል። አሁን መልኩን ቀይሮ የማመቻመች (compromise የማድረግ) ፈተና ሲቀርብ ይታያል። ይህ ከጠላች የውጊያ ስልቶች አንዱ ነው። ቀድሞ በፌዝና በንቀት ተጀመረ፤ ሥራውን ማቆም አልቻሉም። በማስፈራራትና በዛቻም ቀጠሉ፤ አሁንም አልቻሉም። በማሸበርና ጦር በማሰለፍም ለመውጋት ሞከሩ፤ ይህም አልሠራላቸውም። ታዲያ፥ በዚህም በዚያም አልቻልንም፤ አልሆነልንም፤ አልሠራልንም ብለው ተቀመጡ? አልተቀመጡም። ሌላ ሙከራ ሲሞክሩ እናያለን።

1. ጠላት ፊት ለፊት መግጠም ካልቻለ በስውር፥ እንደ ማጅራት መቺ ከጀርባ ለማጥቃት አይሰንፍም።

1፤ እንዲህም ሆነ፤ ቅጥሩን እንደ ሠራሁ፥ ከፍራሹም አንዳች እንዳልቀረበት ሰንባላጥና ጦብያ ዓረባዊውም ጌሳም የቀሩትም ጠላቶቻችን ሰሙ፤ ነገር ግን እስከዚያ ጊዜ ድረስ በበሮቹ ውስጥ ሳንቃዎቹን አላቆምሁም ነበር።

ጊዜውን ተመልከቱ፤ ቅጥሩ ተሠርቶአል፤ ሳንቃ በበር መግባት ብቻ ነው የቀረው። ቅጥሩ ተሠርቶአል፤ እነርሱ ተደብቀው፥ ተሰርቀው መግባት አይችሉም። ሌባ በር አይጠቀምም። በዮሐ. 10፥1 ጌታ እንዲህ አለ፤ *እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው።* በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ ማለት በር ባልሆነ ሌላ መንገድ፥ በግድግዳ ይሁን በጣራ ማለት ነው። ሌባ በበር አይገባምና ስለዚህ እርሱ እንዲወጣ ሲስቡት ነው እዚህ የሚታየው።

ጠላት ማጥቃት ብቻ ሳይሆን የሚያጠቃበትን ጊዜም ይመርጣል። ቅጥሩ አልቋል በር ብቻ ነው የቀረው። በር ካልገባበት ቅጥር ዋጋ የለውም። በር ከሌለው ምኑን ቅጥር ሆነ? በሩ ከገባ ግን ተጠናቀቀ ማለት ነው። አሁን ሊጠናቀቅ ትንሽ ነው የቀረው፤ ታዲያ ያቺ የቀረችው ትንሽ ከመጠናቀቋ በፊት የመጨረሻ ሙከራ ተደረገ። ጠላት እስከ መጨረሻው ተስፋ የማይቆርጥ መሆኑን ጌታን ከፈተነበት ፈተና መገንዘብ እንችላለን። ጌታ አገልግሎቱን ሲጀምር ከተጠመቀ በኋላ በቀጥታ ወደ ምድረ በዳ ነበር የሄደው፤ በፈተና ነበር የተጀመረው። የሰይጣን ዋናው መፈተኛ ቃል፥ ""እግዚአብሄር ልጅ ከሆንክ" የሚል ነበር። ይህ ፈተና በመስቀል ላይ ሲውልም እንኳ ቀርቦለት ነበር። *የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎአልና ከወደደውስ አሁን ያድነው* ይሉ ነበር፤ማቴ. 27፥40-43። በተለይ ይህ የመጨረሻው የስቃይ ጊዜ ነበርና ፈታኝ ሰዓት ነበረ።

እስካሁን ያደረጉትን፥ የተጠቀሙባቸውን ስልቶች ከክርስትና ጉዞ አንጻር ስናጤን፥ <u>መጀመሪያ</u> በንቀትና በፌዝ መጡ፤ ምዕ. 2። ይህ የአዲስ ክርስቲያን መውጊያ ጦር መሣሪያ ነው። <u>ሁለተኛ</u> በፌዝም፥ በንቀትም፥ በዛቻም፥ በማሸበርም፥ በጦር መሣሪያም መጡ፤ ምዕ. 4። ይህ የአዳጊ ክርስቲያን መውጊያ ነው። <u>ሦስተኛው</u> ይህ የአሁኑ ደግሞ የበሳል ክርስቲያን መውጊያ ነው። ጠላት ስልቱ አንድ ብቻ ወይም ሁለት ብቻ አይደለም። ሦስትም አራትም፥ ብዙም ነው። ሲችል ይንዳል፥ ሳይችል ይሸረሽራል፤ ይቆረቁራል። አንዳንዴ ጊዜ ይገዛል፤ የጠፋ፥ የተወ ይመስላል። ተኝቶ የሞተ ይመስላል፤ ግን አለ። አንዳንዴ አዘናግቶ ከጀርባችን ይመታናል።

1. መሪ የሚላማ ጊጤ ነው።

2፤ ሰንባላጥና ጌሳም፥ መጥተህ በኦኖ ቈላ ውሰጥ ባሉት መንደሮች እንገናኝ ብለው ላኩብኝ፤ ነገር ግን ክፉ ያደርጉብኝ ዘንድ ያስቡ ነበር።

አሁን ሕዝቡን ትተው ነህምያ ላይ አተኮሩ። መሪ ከተመታ መንጋ ይበተናል። የንብ ንግሥት ከተያዘች ቀፎው ሙሉ ንብ ይያዛል። በልማዳዊ ጦርነት አዋጊ፥ የጦር መሪ ከሞተ ሠራዊት ይፈታል። ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ከማህዲስቶች ጋር በጎንደር፥ በመተማ እየተዋጉ አባርረዋቸው ሱዳን አገራቸው አስገብተዋቸው ነበር። ማህዲስቶች እርግጥ ተሸንፈው ሊያልቁ ጥቂት ቀርቷቸው ነበር ግን በውጊያው ማብቂያ ላይ መጋቢት 2 ቀን 1881 ዓ. ም. ከፊት ሆነው ሲያዋጉ ሳሉ ንጉሡ ሞቱ። ከዚያ በኋላ ሠራዊቱ ሁሉ ድንብርብሩ ወጣ። እግሬ አውጪኝ ብሎ ማፈግፈግና መሸሽ ጀመረ። በሸሽት ላይ የነበሩት ማህዲስቶች ወደ ኋላ ተመልሰው ኢትዮጵያውያኑን ማሳደድ ያዙ። የሚሸሸው ሠራዊት የንጉሡን ሬሳ እንኳ ሊያድን አልቻለም፤ ጭንቅላታቸው ተቆርጦ ተወሰደ።

አሕመድ ግራኝ በ1530ዎቹ አገሪቱን በሙሉ ወርሮ ነበር። ብዙ ሕዝብ ፈጅቶ፤ ብዙ ንብረት ዘርፎና አውድሞ ነበር። ግን አላረፈም አንድ ነገር እስኪያደርግ፤ ምን? ንጉሡን አግኝቶ እስኪገድል። ግን አልሆነለትም። ንጉሡ በሕይወት ስለነበረ የሕዝቡም ሐሞት አልፈሰሰም። ሁሌም ባይሆን ብዙ ጊዜ መሪ ተሸነፈ ማለት ሕዝብ ተሸነፈ ማለት ነው። ሕዝብ ተበተነ ማለት ነው። ጌታም ስለራሱ መያዝ ሲናገር፥ በማቴ. 26፥31 *በዚያን ጊዜ ሊየሱስ፦ በዚች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ፤ እረኛውን እመታለሁ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ የሚል ተጽፎአልና አለ።* እርሱ ተመታ፤ መንጋው ተበተነ፤ ለጥቂት ጊዜ።

እነ ሰንባላጥ አሁን ሚላማቸው ነህምያ ነው። ነህምያ ከተመታ ከነህምያ መምጣት በፊት ያደርጉ እንደነበረው በሕዝቡ ላይ ጭነታቸውን እንደ ጌኛ ይጭኑበታል። ይህን ለማድረግ ነህምያ ከቅጥር ወደ ውጪ መውጣት አለበት። እንደምንም አሳማኝ ነገር ፈጥረው፥ ተቀባይነት ያለው ምክንያት ፈጥረው፥ አስመስለው፥ እርሱን ማውጣት። ይህ የሰይጣንን ስልት ይመስላል። ሰይጣን ክርስቲያንን ከሸፋኑ፥ ከምሽጉ፥ ከዓለቱ፥ ከዓምባው ማውጣት

ያስደስተዋል። ከወጣ ሜዳ ላይ ያገኘዋል። ሜዳ ላይ ያለ ተዋጊ ጦር ከሁሉም አቅጣጫ ሊጠቃ ይችላል። ከምድር ከየቱም ማዕዘናት ይጠቃል። ከሰማይም ይጠቃል።

ደግሞ እነሰንባላጥ ነህምያው የሚጠሩት ወዴት ነው? ወደ ታች፥ ወደ ቆላ! ከከፍታ ቦታ፤ ከጽዮን ኮረብታ፤ ከኢየሩሳሌም ወደ ታች ወደ መንደሮች። ይህ ምሳሌያዊ አጠራርና ግብጥ ተደርጎ መታየት ይችላል። ዱሮም ጠላት የወረደና የረከሰ ነገር እንጂ ምን ክቡር ነገር አለው? ክቡር እንኳ ቢመስል ወራዳ ነው ፍጻሜው። ከክቡር ጌታ ከራቀ፥ ካራቀ፥ ከተለየ ምንም ክብር የለበትም። ጠላት ቅዱሳንን የሚደልለው በከበረ ነገር ከቶም አይደለም። እርሱ የከበረ ነገር የለውም፤ ግብጥው ወደረከሰና ወደተዋረደ ስፍራ ነው። የእርሱ የመጨረሻ ፍጻሜውም በዚያ ነውና ሁሌም ወደ ቆላ ወደ ታች፥ ወደ ዝቅታ፥ ወደ ወረደ ስፍራ ነው ግብጥው።

ለውይይት **መሪ የጠላት ቀስት ጊጤ ነው። መሪዎች የሆኑ ይህንን ማወቅ የተገባቸው ከምንድን ነው? ከመሪዎች የመጸከይ አስፈላጊነትስ ምን ያህል ሸንደሆነ ተረድተናል? ጠላት መሪዎችን የሚቀስፍባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው? ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕድገትና ብስለት በጨመሩ ልክ የሰይጣን ፈታኝነትና የውጊያ ስልት የሚቀያየረው ከምንድን ነው?**

2. ትልቅ ሥራ እሠራለሁ፤

ነህምያ ምክንያታቸው፥ ዓላማቸው፥ ስልታቸው ገብቶታል። አስተዋይ ነው፤ የጸሎት ሰው ነዋ! ነህምያ ለዚህ ግብጥ ሲመልስ ምን አለ?

3፤ እኔም፥ ትልቅ ሥራ እሠራለሁ፥ እወርድም ዘንድ ላይቻለኝም፤ ሥራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስለ ምን ሥራው ይታጐላል? ብዬ መልእክተኞችን ላክሁባቸው።

እወርድ ዘንድ! በመውረዴ! መዋረድ እንደሆነ ገብቶታል። ሌላ ያለው ቃል አስደናቂ ነው፤ ትልቅ ሥራ እሠራለሁ! የእግዚአብሔር ሥራ ትልቅ ሥራ ነው። ሥራውን ትልቅ ያደረገው ግን የራሱ የሥራው ግዝፈት ሳይሆን የሥራው ባለቤት ትልቅ መሆኑ ነው። በጌታ ቤት ውስጥ ትንሽ ሥራ የለም። ስብከት ትልቅ ሥራ ነው፤ የቡና ቁርስ ዳቦ መጋገርም ትልቅ ሥራ ነው። ማስተማር ወይም መጸለይ ትልቅ ሥራ ነው፤ ውስጥ ልጆች መጠበቅም፥ እውጪ ቢስኪሌትና መኪና መጠበቅም ትልቅ ሥራ ነው።

እስኪ እናስብ፤ የንጉሥ ጸሐፊ ወይም ጠጅ አሳላፊ መሆን እንዴት ትልቅ ነው! የንጉሥ ጸጉር አስተካካይ ወይም እጅ አስታጣቢ መሆንስ? ሥራውን ክቡር ያደረገው ሥራው ብቻውን

ሳይሆን ሥራው የሚደረግለት፥ የአገልግሎቱ ተቀባይ ነው። እየተገለገለ ያለው ንጉሥ ነዋ! የአገልግሎት በራችንን አናጥብብ። ዘመናችን ሳናገለግልበት እንደ ውኃ አይፍሰስ። የአገልግሎት እድል አያምልጠን። የንጉሥ ሥራ እንሥራ። ትልቅ ሥራ እንሥራ። እየሠራን ያለን ጌታ ይባርከን። ጠላት ሥራችንን ሊያንኳስስ ቢሞክር እንንገረው። ሊያስጥለን ቢሞክር እንንገረው። *እኔም ትልቅ ሥራ እሠራለሁ* እንበለው።

ሌላው ነህምያ የተናገረው ቃል፥ "ሥራው ለምን ይታጎላል?" የሚል ነው። ለምን ይቋረጣል ሳይሆን ለምን ይታጎላል። መታጎል ለጥቂት ጊዜ መቆም ነው። ያስ ለምን ይሆናል? ለትንሽ ጊዜስ ቢሆን ለምን ይቋረጣል? ከጠላት ጋር የምናሳልፈው ጊዜ ከጌታ ጋር የምናሳልፈውን ጊዜ ይወስድብናል። በንትርክ የሚያልፍ ጊዜ በግንባታ የሚያልፍ ጊዜን ይሻማል። ለምን ይታጎላል? ለጠላት ቅንጣት ታህል ጊዜስ መስጠት ለምን አስፈለገ? *እኔም ትልቅ ሥራ እሠራለሁ* አለ።

ለውይይት **በዘመናችን ትልልቅ የሚባሉ አገልግሎቶች መለኪያዎች ምን ምን ናቸው? አገልግሎትን ትልቅ የሚያደርገው ምንድን ነው? ጳውሎስ በሮሜ 11፥13-14 አገልግሎቴን አከብራለሁ። ያለው ለምንድን ነው? ሽሻም የንጉሥ ሠራተኞች መሆናችንን ማወቅ በአገልግሎታችን የሚፈጥረው ለውጥ ይኖራል?**

3. ንዝነዛ፥ ሌላው የጠላት ስልት

ከዚያ ምን ቀጠለ? ንዝነዛ። ይህ የጠላት ሌላ ስልት ነው። ጠላት አንዳንዴ እንደ ጎርፍ ይጎርፋል፤ እንደ ፈረሰኛ ወንዝ ይመጣል። ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ ይንጠባጠባል።

4 እንዲህም ቃል አራት ጊዜ ላኩብኝ፤ እኔም እንደ ፊተኛው ቃል መለስሁላቸው።

ዘፍ. 39፥10 የጲጥፋራ ሚስት 'ለዮሴፍ በየዕለቱ ትነግረው ነበር' ተብሎ ተጽፎአል። ለስንት ቀን መሆኑን አናውቅም፤ ግን በየዕለቱ። ነገር ሲደጋገም፣ 'ከሚደጋገምብኝ ላስቁመው' ብለን የተጠየቀውን ልናደርግ እንጋበዛለን። ደሊላ ሶምሶንን ነዘነዘችው፤ መሳ. 16፥16 *ዕለት ዕለትም በቃልዋ ነዘነዘችው አሰቸገረችውም፥ ነፍሱም እስከ ምት ድረስ ተጨነቀች።* ስለ ንዝነዛዋ ምስጢሩን ነገራት። በሉቃ. 18፥5 እንደተጻፈው ዓመጸኛ ዳኛ፤ *ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ሁልጊዜም እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ።* ሰውየው እግዚአብሔርን አይፈራም፤ ሰውንም አያፍርም። ግን ስለ ንዝነዛዋ ፈረደላት። ወይም ሉቃ. 11፥8 ውስጥ

እንደተጻፈው፥ እላችኋለሁ፥ ወዳጅ ሰለ ሆነ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፥ ሰለ ንዝነዛው ተነሥቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል እንደተባለው ሰው ተነሥቶ አደረገ?

ነህምያ አራት ጊዜ ሲላክበት አራቱንም ጊዜ እንደፊተኛው ቃል መለሰላቸው። ምንድርነው የፊተኛው ቃል። ትልቅ ሥራ እሠራለሁ! እወርድ ዘንድ አይቻለኝም። ንዝነዛ፥ ደጋግሞ እንደ ግንደ ቆርቁር አንድ ቦታ መምታት የጠላት አንድ ስልት ነው። ዛፍ ሲጣል ወይም ጠርብ ሲጠረብ አንድ ቦታ ታልሞ ተደጋግሞ እንደሚመታ ማለት ነው። አንድ ጥቃት ሲደጋገም እንንቃ።

4. ሐሜት፥ ሌላው የጠላት ስልት

እስካሁን በቃል ነበር ይልኩበት የነበረው። አራት ጊዜ ከተላከበት በኋላ ከአምስተኛው መልእክት ጋር አብሮት የመጣ ደብዳቤ አለ።

5-7፤ ሰንባላጥም እንደ ፊተኛው ጊዜ ብላቴናውን አምስተኛ ጊዜ ላከብኝ፤ በእጁም ውሰጥ፥ አንተና ኢይሁድ ዓመፅ እንድታሰቡ፥ ሰለዚህም ቅጥሩን እንድትሠራ፥ ንጉሣቸውም ትሆን ዘንድ እንድትወድድ በአሕዛብ ዘንድ ተሰምቶአል። ደግሞም፥ ንጉሥ በይሁዳ አለ ብለው ሰለ አንተ በኢየሩሳሌም ይናገሩ ዘንድ ነቢያትን አቁመሃል፤ አሁንም ለንጉሥ ይህን ቃል ያወሩለታል፤ እንግዲህ መጥተህ በአንድነት እንማከር የሚል ክፍት ደብዳቤ ነበረ።

ደብዳቤው ክፍት ደብዳቤ ነው። ክፍት ደብዳቤ ማለት ወይ ሥልጣን የሌለው ደብዳቤ ነው። ወይም ለአሉባልታና ማንም እንዲያየው፥ እንዲያነብበው ሆን ብሎ ክፍት እንዲሆን የተደረገ ደብዳቤ ነው። የባለ ሥልጣን ደብዳቤ የንጉሡ ማኅተም አለበት። በሰም የታሸገና በሰሙ ላይ በንጉሡ ቀለበት የታተመበት ነው። ክፍት የሆነው ነህምያ ክፍት ደብዳቤ መሆኑን ሲያውቅ፥ ይህ በሰምና በማኅተም ያልታሸገ ደብዳቤ ይኸኔ በስንት ሰው ተነብቦ ይሆን? ስለዚህ ሌሎችም ያወቁት ጉዳይ ስለሆነ መልስ ለመስጠት ሄጄ እንዳሉኝ መመካከር አለብኝ እንዲል ይሆናል። ደግሞ ለንጉሡ ያሰቡም ይመስላሉ። ግን ሐሜት ባይሆንና እርግጠኛ የሆነ የተጨበጠ ነገር ቢኖር ወደ ንጉሡ ይልኩ ነበር። አልላኩም። ትልልቅ ቃላት ነው የተጠቀሙት። ዓመጽ እንደታሰበ፥ ንጉሥ የመሆን አሳብ እንዳለ፥ ስለራሱ የሚናገሩ ነቢያት እንዳቆመ ተጽፎበታል። እነዚህ ነገሮች ለሚደነግጥ ሰው ያስደነግጣሉ።

ለነህምያ ግን ምኑም አይደሉም። ራሱን ያውቃላ! ሥራውን ያውቃልና፥ ሥራው ያልሆነውንም ያውቃልና፥ ትክክለኛ ነውና፥ ጻድቅ ነውና፥ እንደ አንበሳ ተዘልሎ ተቀመጠ። ሰዎች ለሚፈጥሩትና ለሚያወሩት ሐሜትና አሉባልታ ጊዜም፥ ስሜትም፥ ጉልበትም አናባክን። በቀጥታ ለመጣው መልስ እንስጥ። እንደ ሐሜት በዙሪያ ጥምጥም ለመጣው ግን መልስም አለመስጠት ብቻ ሳይሆን ለመስጠት በማሰብ ጊዜ ማባከንም ኪሳራ ነው። ሰዎች ለሚያወጉት ወግና ለሚፈጥሩት ሐሜት ቦታ አትስጡ። ሐሜተኞች እውነት አይናገሩም፤ እውነተኞች ደግሞ አያሙም። ፊት ለፊት ነው የሚናገሩት። ሐሜት የነገሩ ባለቤት በሌለበት ስለዚያ ሰው መናገር ነው። "እንዲህ አስበሃል፤ እንዲህ ይወራል፤ እንዲህ አልክ ተብሎ

በአሕዛብ ዘንድ ተሰምቶአል፤ ይህ ነገር ወደ ንጉሡ ሊሄድ ነው . . . ምን ትላለህ? ናና እንማከር” ነው የሚሉት። ነህምያ ግን ወይ ፍንክች!

የነህምያ መልስ ምን ነበር?

8፤ እኔም፥ አንተ ከልብህ ፈጥረኽዋል እንጂ እንደ ተናገርኽው ነገር ምንም የለም ብዬ ላክሁበት።

እርሱ መፍጠሩን በምን ያውቃል? በአንድ ነገር እርግጠኛ በመሆኑ ያውቃል፤ ያም የተባለው ነገር ሁሉ ውሸት መሆኑን፥ በእርሱ ልብ ውስጥ የሌለ መሆኑን ያውቃል። የልቡን ንጽህና ያውቃል። ከእግዚአብሔር በታች ከልብ የሚበልጥ ፈራጅ የለም። ከኅሊና በላይ ዳኛ የለም። ጳውሎስ እውነቱን ነው ለንጹሕ ኅሊና የተጋው! *ሰለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ* ሐዋ. 24፥16። ነህምያ ልቡን ያውቀዋልና እንዲህ ያለው ጉድፍ ከየት እንደሚመነጭ ያውቃል።

በኅሊናው ብቻ ሳይሆን በአምላኩም መታመን የነህምያ ልማድ ነውና ወደ አምላኩ ደግሞ በዚህ ጉዳይ ቀረበ።

9፤ እነርሱም ሁሉ ሥራው እንዳይፈጸም፥ እጃቸው ይደክማል ብለው ያስፈራሩን ዘንድ ወደዱ፤ አሁንም፥ አምላክ ሆይ፥ እጄን አበርታ።

የተነጻጸሩትን ቃላት አስተውሉ፤ እነርሱ እጃቸው ይደክማል አሉ፤ አንተ ደግሞ እጄን አበርታ አለ። የጸሎት ሰው። በየአጋጣሚው፥ በየምክንያቱ አምላኩን የሚጠራ የጸሎት ሰው ነው ነህምያ።

ለውይይት **እነዚህ ሰዎች ወደ ነህምያ አነታትከው መላካቸው፥ ደጋግመው መነዝነዛቸው ለምንድን ነው? ነገር ሲደጋገም የሚያመጣው ለውጥ ምንድን ነው? ሐሜት ማለት ምን ማለት ነው? ከነህምያ የተላከለት ደብዳቤ ክፍት መሆኑ ምንን ያመለክታል? ባለቤት የሌለው ሐሜት በምናገኝበት ጊዜ ምን ማድረግ አለብን?**

5. ሌላው የጠላት ስልት፥ ሐሰተኛ ትንቢትና የግዢ አገልግሎት

የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚመስል፥ መንፈሳዊ መልክ ያለው፥ አስመሳይ ነገር በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሊሠለጥን ይችላል! እዚህ ጎልቶ የሚታየው ሸማያ የተባለው ሰው ነው። ግን ብቻውን አልነበረም ኖዓድያ የተባለች ሴት ነቢይት አለች፤ ሌሎችም በስም ያልተጠቀሱ ነቢያት አሉ። የሁሉም ግብ አንድ ነው ነህምያን ማስፈራራት ነበር።

10፤ እኔም ወደ መሔጣብኤል ልጅ ወደ ድላያ ልጅ ወደ ሸማያ ቤት ገባሁ፤ እርሱም ተዘግቶ ነበርና። በእግዚአብሔር ቤት በመቅደሱ ውስጥ እንገናኝ የመቅደሱንም ደጆች እንዝጋ፤ እነርሱ መጥተው ይገድሉሃልና፥ በሌሊትም ይገድሉህ ዘንድ ይመጣሉና አለ።

ይህ ሸማያ መሰሪ ሰው ነው። በቤቱ ውስጥ ቤቱን ዘግቶ የነበረ ሰው ነው። *እርሱም ተዘግቶ ነበርና* የሚለው ቃል ምንነት ግልጽ አይመስልም። ምናልባት ቤቱ ተዘግቶአል። ወይም ሰውየው ቤቱን በራሱ ላይ ዘግቶአል። ምናልባት መደበቅን ወይም ጥሞናን ሊመስልም ይችላል። ሁለቱም ነህምያን በቀላሉ መሳብ ይችላል። መደበቅ ከሆነ እርሱም ከነህምያ ጋር የጋራ ጠላት እንዳለው ለማስመሰል ነው። ራሱን በቤቱ የዘጋ ሰው መምሰሉ ደግሞ ምናልባት መንፈሳዊ እንደሆነ ለማስመሰልም ይሆናል። በዘመኑም በኛም ዘመን አንዳንድ ነቢያትና የእግዚአብሔር ሰዎች የሚባሉ ራሳቸውን በቤታቸው ይዘጉና ወይም ይመሸጉ መንፈሳዊ መስለው ለመታየት ገብተው አይወጡም። ከእግዚአብሔር ጋር የሰመረ ግንኙነት ያላቸው ለመምሰል፤ ለእግዚአብሔር የተጠጉ፥ የቀረቡ፣ እርሱን የሚሰሙ፥ የሚያደምጡ፥ የጥሞና ጊዜ ያላቸው ለመምሰል የዘጉ ሰዎች ናቸው። አንዳንዶቹ እውነትም ለመልካም የጥሞና ጊዜ ይዘጉ ይሆናል። ወደ ቤት ወደ እልፍኝ ገብቶ በርን በኋላ መዝጋትና ከጌታ ጋር መሆን መልካም ነው፤ ጌታም አስተምሮታል፤ መዝጋትህ ግን መታወቅ የለበትም። በስውር የሚያይ አባትህ በግልጽ እንዲከፍልህ ጸሎትህም በስውር መሆን አለበት እንጂ በር መዝጋትህ መለከት ተነፍቶ ማርሽ ተመትቶ በአዋጅ መሆን የለበትም። ግብዝነታቸውና ለመታየት ማድረጋቸው፥ ለመሳብና ለማጥመድ ማድረጋቸው ቢቆይም ሳይገለጥ አይቀርም። የዚህ ሰው ቤት ከመዘጋቱ ወይም ራሱ ወደ ቤቱ ገብቶ ከመዝጋቱ ሌላ የታወቀ ነገር የለም። ወጥመድ እንደሆነ ግን ይስተዋላል።

ነህምያ ለምን ወደዚህ ሰው ቤት ለምን እንደገባ አናውቅም። ወይ ቀድሞ በጥሩ ይተዋወቁ ይሆናል። ምናልባት እውነትም መንፈሳዊ ሰው ሆኖ አብረው እንዲጸልዩ አስቦም ይሆናል። አናውቅም። ግን ገባ። ሸማያ የሰጠው ምክር ግን ነህምያ ያልጠበቀው ምክር ነበር። ወደ መቅደስ እንዲገባ፥ ደጆቹን እንዲዘጋ፥ እንዲሸሸግ መከረው። ምክሩ ከውጭ ሲታይ መልካም ይመስላል። አስቦለት የተናገረለት ይመስላል። መልካም የጥበቃ ምክር ይመስላል። ግን መልካም የሚመስል ሁሉ መልካም አይደለም። አይደለም! ምሳ. 14፥12 እና 16፥ 25 *ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው* ይላል። ለሰው ቅን የምትመስለውን ግን ያልሆነችውን መንገድ እንዴት እናውቃለን?

መልካም የሚመስለውን ለይቶ ለማወቅ መልካም የሆነውን አጥርቶ ማወቅ ያስፈልጋል። ይህን ለመረዳት ደግሞ ጸሎት ጉልህ ስፍራ አለው። ነህምያ የጸሎት ሰው ነው። ለራሱ

የሰጠው ስፍራ ደግሞ ትክክለኛ ስፍራ ነው። ራሱን ቆጥ ላይ አላስቀመጠም። ሰዎች ራሳቸውን የተለየ የከበረ ስፍራ ላይ ሲያስቀምጡ ነው በዙሪያቸው መሸፈኛ፥ ዘበኛ፥ መደረቢያ ቡልኮ የሚፈልጉት። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እንደ ርእሰ ብሔር በአጃቢ፥ ያውም የደንብ ልብስ በለበሱና ጥቁር መነጽር ባደረጉ፥ ምናልባትም በታጠቁ ሰዎች ታጅበው የሚሄዱ ቴያትረኛ ሰባኪዎች በአገራችን መቆጠር ጀምረዋል። እንዲህ ያሉት ታጃቢዎች ይህን የሚያደርጉት ወይ ለጉራ ነው፤ ወይም በእግዚአብሔር ጠባቂነት እምነት ስለሌላቸው ነው። ነህምያ ራሱን ያወቀ፥ ስፍራውን ያወቀ፥ ሥራውንና ጥሪውን ያወቀ፥ ተልእኮውን ጠንቅቆ የተገነዘበ ሰው ነው።

፲፤ እኔም፥ እንደ እኔ ያለ ሰው የሸሸና፥ ነፍሱንስ ያድን ዘንድ ወደ መቅደስ የገባ ማን ነው? እኔስ አልገባም አልሁት።



እንደ እኔ ያለ ሰው! ነህምያ ሊነግሥ አልመጣም። ሊሠራ ነው የመጣው። ከልቡ መሪም ነውና እየመራም ነው። መሪ ሆኖ ከሸሸ ምኑን መሪ ሆነ? በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን የመሪነት ሞገስ ከነፈጋቸው ጊዜዎች አንዱ በጣሊያን ወረራ ወቅት ከአገሪቱ መውጣታቸው ነው። እርግጥ ክርክር ተደርጎ ነበር፤ በክርክሩ አንዳንዶች፥ ለምሳሌ፥ እንደ ታከለ ወልደ ሐዋርያት ያሉት በጥንካሬ ተቃውመዋል። ንጉሡ መውጣታቸው ቢወሰንም ውሳኔው ሙሉ ስምምነት ያለበት አልነበረም። በመጨረሻ ራስ እምሩ እንደራሴ ተደርገው ንጉሡና ቤተ ሰባቸው ሲወጡ፥ ☒መሪ ሸሸ☒ተባለና ጥቁር ነጥብ ሆነ። በአንጻሩ ደግሞ፥ በዚያኑ ዘመን አቡነ ጴጥሮስ ለመሸሽ ወይም ለጣሊያን ለማደር ዕድል ኖሮአቸው አላደረጉትም። ውግዘቱንና ግዝቱን ስለደረደሩና ግዝቱን እንዲያነሡ ተጠይቀው አልፈታ ስላሉ በጥይት ተደብድበው ሞቱ። መሪ አይሸሽም። በኮሎኔል መንግሥቱ መንግሥት የተገደሉት የመካነ የሱሱ መሪ ቄስ ጉዲና ቱምሳ በውጭ አገር ተቀማጥለው መኖር ይችሉ ነበር፣ ዕድሉም ነበራቸው፤ ግን መሪ ነበሩና ሕዝቡን ጥለው ወዴት ይሂዱ? አልሄዱም፤ ተይዘው ተወሰዱ፤ ተገደሉ። በደርግ ዘመን መጨረሻ ኮሎኔል መንግሥቱ ያደረጉትም አስተዛዛቢ ነገር ነበረ። በቀውጢ ሰዓት መሪ ሕዝቡን ሲተው፥ ራሱን ሲያድን፥ ከአገር ሲወጣ ውድቀት ነው። መሪ ሲሸሽ ትልቅ አደጋ ነው።

ነህምያ ይህን የተገነዘበ ሰው ነውና ለሐሰተኛው ነቢይ ምን አለ? *እንደ እኔ ያለ ሰው የሸሸና፥ ነፍሱንስ ያድን ዘንድ ወደ መቅደስ የገባ ማን ነው? እኔስ አልገባም አልሁት* አለ። እኔስ አልገባም! ሌላ ያድርግ እንጂ እኔስ አላደርገውም አለ!

ሌላው አስገራሚ ነገር ነህምያ የመለየት ስጦታ ያለው ሰው ነው። መናፍስትን መለየት ተብሎ በአዲስ ኪዳን እንደተጠቀሰው ያለ ስጦታ ያለው ይመስላል። *አወቅሁ* አለ። ምን አወቀ? ይህ ሸማያ የተባለው ሰው ትንቢት እንደተናገረ፥ ግን እግዚአብሔር እንዳልላከው አወቀ። የጌታ የሆነውን የጌታ ካልሆነው ለይቶ ማወቅ እንዴት ድንቅ እውቀት ነው! የጌታ ያልሆነውን የጌታ ከሆነው ለይቶ የማወቁ አንድና ብቸኛ መንገድ የጌታ የሆነውን ጠንቅቆ ማወቁ ነው። የጌታ

የሆነውን የምናውቅበት ብቸኛው መንገድ ደግሞ ቃሉን ማወቅ እና የጸሎት ሰው መሆን ነው።

እግዚአብሔር ሳይልካቸው ትንቢት የሚናገሩ ያኔ ነበሩ፤ አሁንም አሉ። ግን ነህምያ እንዳወቃቸው እኛም እንድናውቃቸው መንፈስ ቅዱስ ያግዘን። እንድናውቃቸው ደግሞ ማድረግ ያለብን ሐሰተኛውን ለማወቅ እውነተኛውን ነገር ማወቅ ነው። ቃሉን ስናውቅ ነቢያት ነን የሚሉ ሰዎች፥ የእግዚአብሔር ቃልና ልዩ መልእክት አለን የሚሉ ሰዎች ሲናገሩ ሳንደናገር ማወቅና መለየት እንችላለን። ነህምያ አወቀ።

12-13፤ እግዚአብሔርም ልኮት እንዳልነበረ፥ በእኔ ላይ ግን ትንቢት እንደ ተናገረ፥ እነሆ፥ አወቅሁ፤ ጦብያና ሰንባላጥም ገዝተውት ነበር። ይህንም ነገር አደርግና እበድል ዘንድ፥ በእኔም ላይ ክፉት እንዲናገሩና እንዲያላግጡ ያሰፈራራኝ ዘንድ ተገዝቶ ነበር።

ያወቀው ደግሞ ሐሰተኛ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ተገዝቶ እንደነበረም ነው። ይህ የትንቢትና የነቢይ ሽቀጥ መሆን ሌላው አሳዛኝና አሳፋሪ ነገር ነው። *ጦብያና ሰንባላጥም <u>ገዝተውት ነበር</u> ደግሞም ይህንም ነገር አደርግና እበድል ዘንድ፥ በእኔም ላይ ክፉት እንዲናገሩና እንዲያላግጡ ያሰፈራራኝ ዘንድ <u>ተገዝቶ ነበር</u>* ይላል። ነቢይና ትንቢት በገንዘብ ሲገዛ፥ ጸጋ ሲቸበቸብና ማትረፊያና መኖሪያ ሲደረግ ያሳዝናል፤ ያሳፍራል።

ይህ በ2ጴጥ. 2፥15 የበለዓም መንገድ የተባለው ነው፤ ጴጥሮስ ስለ ሐሰተኞች ሲናገር፥ *ቅንን መንገድ ትተው ተሳሳቱ፤ የባሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ፤* እርሱ የዓመፃን ደመወዝ ወደደ ይላል። ይሁዳም በይሁ. 11 ደግሞ *ወዮላቸው፥ በቃየል መንገድ ሄደዋልና ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል* ይላል። ለገንዘብ ሲባል ትንቢት ይተነበያል። ለገንዘብ ሲባል መባረክም መርገምም ይደረጋል! ማቴ. 23፥14 *እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ፥ ወዮላችሁ፤ ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ* ይላል። አይገርምም በጸሎት ርዝመት የመበለቶችን ቤት ማራቆት? ጸሎት በዘመናችን የገንዘብ መሥሪያም ሆኗል። በጸሎት ስም ?ስት ሃውስ?እየተባለ መንግሥትም ቅዱሳንም የማያውቁት ምዝበራ ይካሄዳል።

እንዲህ ሲሆን ምን መደረግ አለበት? መጸለይ የመጀመሪያው ነገር ነው። ውጊያው መንፈሳዊ ነውና ጉዳዩን ወደ ጌታ ማቅረብ ተገቢ እርምጃ ነው። ነህምያ ጸለየ።

14፤ አምላኬ ሆይ፥ ስለዚህ ሥራቸው ጦብያንና ሰንባላጥን ያሰፈራሩኝም ዘንድ የወደዱትን ነቢይቱን ኖዓድያን የቀሩትንም ነቢያት አሰብ።

ከመጸለይ ጋር መግለጥም ተገቢ ነው። አንድ ሽማያ ብቻ አይደለም። ኖዓድያ የተባለች ሴት ነቢይት አለች። የቀሩትንም የተባሉ ሌሎች ደግሞ አሉ። ሌሎችም ነው የተባለውና ቢያንስ ሁለት አሉ። አንድ ላይ ቢያንስ አራት ሐሰተኛ ነቢያት አሉ። እነዚህን በስም መጥቀሱ ማንነታቸውን ከነሥራቸው መግለጡ ነው። መጸለይና በመንፈስ መዋጋት አንድ መንገድ

ነው። እርግጠኛ ስንሆን መግለጥ ሌላው መንገድ ነው። መግለጥ ሌሎችን እንዳይጠቁ የመከላከያው መንገድ ነው።

ሐሰተኛ ትንቢትና ሐሰተኛ ነቢያት የጌታ ሥራ ማስናከያ አንድ መሣሪያ ናቸው። እንወቃቸው፤ እንጠንቀቅ፤ እንግለጥ።

ለውይይት ሐሰተኛ ነቢያት የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ የሚጎዱት እንዴት ነው? ሐሰተኛ ነቢያት ነገንዘብ ጋር ያላቸው ቁርኝትስ ምን ይመስላል? መሪዎች ነመንጋቸው የተለዩና ራሳቸውን ከመጠበቅ የሚጥሩ የመሆናቸው ጎጂነት ምን ያህል ነው? እንዴት?ሐሰተኛ ነቢያትን በስም መጥቀስና መግለጥ ጥቅም አለው ወይ ጉዳት? እንዴት?

6. ሌላው የጠላት ጥቃት መስኮት የሥጋ ዝምድናን ከመንፈሳዊው ማስበለጥና የሥጋ ሥራን መሥራት፥ ወገናዊነት መንፈሳዊነትን ሲሸፍን ነው።

17-19፤ ጦብያም የኤራ ልጅ የሴኬንያ አማች ሰለ ነበረ፥ ልጁም ይሆሐናን የቤራክያን ልጅ የሜሱላምን ሴት ልጅ ሰላገባ፥ በይሁዳ ብዙ ሰዎች ከእርሱ ጋር ተማምለው ነበርና በዚያ ወራት ብዙ የይሁዳ አለቆች ወደ ጦብያ ደብዳቤዎች ይልኩ ነበር፥ የጦብያም ደብዳቤዎች ወደ እነርሱ ይመጡ ነበር። ደግሞም በፊቴ ሰለ እርሱ መልካም ይናገሩ ነበር፥ ቃሌንም ያወሩለት ነበር፤ ጦብያም ሊያሰፈራራኝ ደብዳቤዎችን ይልክ ነበር።

ጦብያ አምቻና ጋብቻ ሆኖአል። ከብዙ የይሁዳ ሰዎች ጋር ተማምሎአል። ከይሁዳ አለቆች ጋርም ደብዳቤ ይላላክ ነበር። መላላኩን ነህምያን ለማስፈራራት ተጠቀመበት። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የዝምድና፥ የጓደኝነት፥ የወዳጅነት፥ የጥቅም ነገር ሲገባ ያስደንቃል።

በመጀመሪያ መጋባታቸው ያስደንቃል። አይሁድ በግልጽ ከተነገሩአቸው ነገሮች አንዱ ከአሕዛብ ጋር በጋብቻ እንዳይጠመዱ ነው። እነዚህ ተጋቡ፤ ተጣበቁ። አይሁድ ከአሕዛብ ጋር እንዳይጋቡ የተከለከሉት በጋብቻው ውስጥ እነርሱ ተሸናፊ እንደሚሆኑ የታወቀ ስለሆነ ነው። ቀድሞውኑ ወደዚያ ጋብቻ ለመግባት የፈለጉት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት የላላ በመሆኑ ነው። ከአሕዛብ ጋር መጋባት ማለት ልክ ማጥ ውስጥ ያለ ሰውን ለማውጣት እማጡ ውስጥ እንደመግባት ነው። በክርስቲያናዊ ጋብቻም ጉዳዩ ተመሳሳይ ነው። ከዓለም ለመውጣት ከፈቀዱ ገመድ እንወርውርላቸው እንጂ፥ የቃሉን እውነት ነግረን ለመውጣት ፈቃደኛ ይሁኑ እንጂ ካሉበት ለማውጣት ብለን እጃችንንም አናጠላልፍ። ከስር ያሉት እነርሱ መሆናቸውን አንርሳ።

መጋባታቸው ሳያንስ እነዚህ ሰዎች ለጦብያ ወሬ አቀባዮችና ጠበቃዎች ሆነዋል። የእግዚአብሔርን ቤት ለማፍረስ መሣሪያ ሆነዋል። እነዚያ ይገነባሉ፤ እነዚህ ደግሞ የሚያፈርሱትን ይረዳሉ፤ ያግዛሉ። በጌታ ቤት ውስጥ ሆነው ከመገንባት ይልቅ የሚያፈርሱ መኖራቸው ያሳዝናል። ጌታን በማስከበር ፈንታ ስሙን የሚያሰድቡ መኖራቸው ያሳዝናል። እንዲህ ከመሆን እግዚአብሔር ይታደገን።

7. በጥቃት ውስጥም የጌታ ሥራ ይጨረሳል፤ ይፈጸማል። አድራጊው ደግሞ እርሱ ነው።

15-16፤ ቅጥሩም በኤሉል ወር በሀያ አምስተኛው ቀን በአምሳ ሁለት ቀን ውስጥ ተጨረሰ። ጠላቶቻችንም ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ በዙሪያችን የነበሩ አሕዛብ ሁሉ ፈሩ፥ በራሳቸውም አሳብ እጅግ ተዋረዱ፥ ይህም ሥራ በእግዚአብሔር እንደ ተደረገ አወቁ።

ሀ. የጌታ ሥራ በጅምር አይቀርም። ጥቃት ቢኖርም ይጨረሳል። ፈሪ አይሠራም፤ ሠሪ አይፈራም። የፈሩ ሰዎች ነበሩ፤ ግን እነ ነህምያ ፈሪዎች አልነበሩም። ስለዚህ ሠሩ። ሥራው ተጨረሰ። የጌታ ሥራ በእርሱ አሳብ ከተጀመረ ይጨረሳል። በ52 ቀን ይሁን በ52 ወር ወይ በ52 ዓመት ግን ይጨረሳል! *በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና፤* ፊል. 1፥6። ጉዞአችን ይፈጸማል። ቤታችን እንደርሳለን። ወጀቡ ቢበዛም፥ ጀልባችን ብትንገላታም በሰላም ወደ ማዶ እንሻገራለን። ሰው እንኳ ጀምሮ የሚጨርስ የሚያጠናቅቅ ከሆነ እግዚአብሔርማ እንዴታ! ያስጀመረንን ያስጨርሰናል። ይህን የሕይወትም የአገልግሎትም ጉዞ ያልጀመርንስ? ካልጀመርን አንጨርስምና እንድንጨርስ እንጀምር?

ለ. አድራጊው እግዚአብሔር ነው። ይህም ሥራ በእግዚአብሔር እንደተደረገ አወቁ! የእግዚአብሔር ሥራ በሰዎች አማካይነት ይሠራ እንጂ ሠራተኛው ክብርና ሞገስ የሚወስድበት ጉዳይ አይደለም። እስካሁን የምናየው ነህምያ ሲመራና ሲሠራ፥ ሰዎቹ ሲለፉና ሲሠሩ፥ ሲዋጉና ሲተጉ ነው። ግን ነህምያ የጌታውን ምስጋና ወስዶ ለሰዎች የሚሰጥ ሰው አይደለም። *ይህም ሥራ በእግዚአብሔር እንደ ተደረገ አወቁ።* እግዚአብሔር ከኛ ጋር ባይሆን . . . መዝ. 124።

እግዚአብሔር ካላደረገ የሰው ብቻ ሥራ ነው። *እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር፤* እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም። 1ቆሮ. 3፥6። በሥራችን በመከናወናችን መጨረሻ ክብርን ለጌታ የምንሰጥ ሰዎች ነን? በእግዚአብሔር ተደረገ ብለን የምናስብል ሰዎች ነን?

ለውይይት

ነሀ. 6ን ከማጠቃለል፤ ጠላት ፊት ለፊት መግጠም ካልቻለ በስውር ከማጥቃት አይሰንፍም። በአሳቻ ቦታ፥ በድንገተኛ ጊዜ፥ አድፍጦ መምታት ልምዱ ነው። እናስተውለዋለን? መሪ የሚለማ ጊጤ ነው። መሪዎች ነሆንን ይህን አውቀናል? ያልሆንንስ ከመሪዎች እንጸልያለን?ሥራችንን ስናየው ትልቅ ላይመስል ይችላል፤ ግን ሥራው የትልቁ ጌታ ሥራ ነው። ንዝነዛ፥ ሌላው የጠላት ስልት። ደጋግሞ እንደ ግንደ ቆርቁር አንድ ቦታ መምታት። አንድ ጥቃት ሲደጋገም እንንቃ። ሐሜት የጠላት ሌላ ስልት ነው። ሐሚተኛ ሰው እውነት አይናገርም፤ እውነተኛ ሰው አያማም። የትኛው ነን? ሌላው የጠላት ስልት፥ ሐሰተኛ ትንቢትና የግዚ አገልግሎት ነው። ጸጋና ስጦታን በገንዘብም የሚቸበችቡ ሰዎች እንደሚኖሩ እናስተውላለን? በእግዚአብሔር ስምም መነገድ እንዳለ እናስባለን? በጌታ ቤት የሥጋ ዝምድናን፥ የወዳጅነት፥ የጓደኝነት፥ የሽርክናና የንግድ ሥራን መሥራት የሥጋ ሥራን መሥራት ነው፤ መንፈሳዊው ነገር የሚበልጥብን ነን? የጌታ ሥራ ይጨረሳል፤ ይፈጸማል። በሥራችን በመከናወናችን መጨረሻ ክብርን ለጌታ የምንሰጥ ሰዎች ነን?